ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቅጽ 02 ቁ.13
የካቲት 2018 ዓ.ም



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብርጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation - Parliaments. Peace. Policy

## መልክዓ - ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው :: ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው ::

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፡- ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ።
- አዲስነት፡- ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፡- ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል


+251 99 808 5013

+251 115 57 74 96

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

UNECA, SA Building, 9th Floor,

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.

# ማውጫ


**የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ የካተት ክራሞት** ..... 2

**በወሩ የተካሄደ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ** ..... 2

**1. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት** ..... 3

አስረጂ መድረኮች ..... 3

**2. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር** ..... 6

የተቋማት ሪፖርቶች ..... 6

የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች ..... 10

የመስክ ጉብኝቶች ..... 10

**3. የውክልና ሥራዎች** ..... 12

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ መራጮች ምን ጉዳዮች አሳሰቡን አሉ? ..... 12

ከሲዳማ የተሰማው ..... 14

ከኦሮሚያስ... ..... 15

የሱማሌ ክልሉ መድረክ ..... 17

ወደ አማራ ክልል. . . ..... 17

አዲስ አበባስ ምን አለች? ..... 18

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መራጮች ለእንደራሴዎቻቸው ምን አነሱላቸው? ..... 19

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዜጎች ምን አሉ? ..... 20

ወደ አፋር ስንሻገር... ..... 20

**4. የፓርላማው ዲፕሎማሲ** ..... 22

**5. እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው በ'ራሳቸው** ..... 24

**6. እንደራሴዎቹ እና ምርጫ 2018** ..... 26

**7. የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ በአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ** ..... 27

ለምን ወደ ምክክር? ..... 27

ኢትዮጵያን ወደ ብሔራዊ ምክክር የመራት ምንድር ነው? ..... 27

ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ፦ የጎርዲያኑ ቋጠሮ? ..... 28

ምን ተብሎ ነበር? ..... 30

ለምን ይራዘምልንስ አሉ? ..... 31

ትችቶቹ ምንድር ናቸው? ..... 32

የብሪጅ ምክረ-ሐሳቦች ..... 33

የምክክሩን ሂደት የሚያሳልጡ ቁልፍ ተግባራት ..... 34

# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የወርኃ የካቲት ክራሞት

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ የካቲት ተለምዷዊ የሆኑትን ሕገ-መንግሥታዊ ተግባራቶቻቸውን አከናውነዋል። በዚኽ ወር ያደረጉት መደበኛ ስብሰባ አንድ አስቸኳይ ስብሰባ ብቻ ነበር። ከዚያ ባለፈ ወሩ የካቲት እንደመሆኑ፣ ከሐምሌ እስከ መስከረም መጨረሻ ድረስ ከሚያካሂዱት የውክልና ሥራ በተጨማሪ፣ ከየካቲት አንድ አንስቶ እስከ የካቲት ሠላሳ ድረስም እንዲኹ የውክልና ሥራቸውን የሚከውኑበት መሆኑ ይታወቃል። ከዚኽ አኳያም፣ በዚኹ ወርኃ የካቲት በዛ ያሉ እንደራሴዎቻቸውን ወደ ተመረጡባቸው የምርጫ ክልሎች በመላክ፣ ዜጎች ያሳስቡናል ባሏቸው ከመልካም አሥተዳደር እስከ የባሕር በር አኹነኛ ኹኔታ፣ ከመሠረተ-ልማት እስከ ጸጥታ እና የሰላም ጉዳዮች መራጮቻቸውን አወያይተዋል። ይኽች የብሪፎ ቅጽ ኹለት ዐሥራ ሦሥተኛ ዕትምም፣ እኒኽን ጉዳዮች በመልክ በመልካቸው አጠናቅራ እና የወሩን የብሪፎ ዳሰሳዊ ምልከታ አካታ እንዲኽ ተጠንቅራለች።

## በወሩ የተካሄደ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ

| 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን | ቀን | አጀንዳ |
|---|---|---|
| **1ኛ አስቸኳይ ስብሰባ** | የካቲት 11 | በአገራዊ ምክክር ኮሚሽን የእስከአኹን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ መወያየት፤ |

## 1. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

እንደራሴዎቹ፣ በወርኃ የካቲት ያጸደቋቸው ሕግጋትም ሆኑ የመሯቸው ረቂቅ ዐዋጆች አልነበሩም። ያም ቢሆን፣ በሦሥት ዐዋጆች ዙሪያ የአስረጂ መድረኮችን አካሂደዋል።

### አስረጂ መድረኮች

በወርኃ የካቲት በቀዳሚነት የተካሄደው የአስረጂ መድረክ፣ **የፌዴራል የስፖርት ልማት እና አሥተዳደር ረቂቅ ዐዋጅን** የተመለከተው ነበር። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ረቂቅ ዐዋጁን አስመልክቶ ከባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጋር የአስረጅዎች መድረክ አካሂዷል። የዐዋጁን መሻሻል አስፈላጊነት ጨምሮ ማብራሪያ ያስፈልጋቸዋል እንዲኹም በረቂቅ ዐዋጁ ውስጥ ሊካተቱ ይገባቸዋል ተብለው ለተነሱ ሐሳቦች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ማብራሪያ ሰጥቶባቸዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ማሞ፣ ስፖርት በሕዝቦች ዘንድ ፍቅር፣ ሰላም፣ መቻቻል እና ወንድማማችነትን በመፍጠር ማኅበራዊ መስተጋብርን ከፍ የሚያደርግ እንደሆነ ገልፀው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ስፖርት በሕግ፣ በሥርዓት እንዲመራ የሚያስችል እንዲሆን ቋሚ ኮሚቴው በጥልቀት እንደመረመረው መናገራቸው ተዘግቧል። የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ሸዊት ሻንካ በኩላቸው፣ ስፖርት ትልቅ ኢንዱስትሪ እና ብዙ ሃብት የሚያንቀሳቅስ መዋዕለ-ንዋይ በመሆኑ ግልፅ የሆነ አሠራር በመዘርጋት በሕግ መምራት እንደሚያስፈልገው ገልፀዋል። ሚኒስትሯ ለጥቀውም፣ ረቂቅ ዐዋጁ የተለያዩ አገራትን ተሞክሮ በመውሰድ የዘርፉ ምሁራን የተሳተፉበት ጥናት የተደረገበት በመሆኑ፣ በዘርፉ ላይ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችን እና የመልካም አሥተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ያስችላልም ብለዋል።

ይኸው ቋሚ ኮሚቴ በዚኹ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ አስመልክቶ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተጨማሪ ከተጠሪ ተቋማትም ጋር ውይይት ማድረጉ ሲዘገብ፤ ቢሾፍቱ ከተማ ላይ እንደራሴዎቹ በረቂቁ ላይ እንዲወያዩበትም መድረክ ተዘጋጅቶ ነበር ተብሏል። በዚያ መድረክ ላይ የተገኙት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ፣ በስፖርት ዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ በሳይንሳዊ እና በዘመናዊ መንገድ መምራት እንዲቻል የዐዋጁ መሻሻል አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ተናግረዋል።

ቋሚ ኮሚቴው፣ የተጠቀሰውን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ጨምሮ የክልል ምክር ቤቶች አፈ-ጉባኤዎች እና የምክር ቤቶቹ ማኅበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲኹም የስፖርቱ ዘርፍ የሥራ ኃላፊዎች ጋርም በረቂቁ ዙሪያ ውይይት ማድረጉን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡርቃም፣ የምናወጣው ዐዋጅ ከትችት የፀዳ ብሎም ዘመን ተሻጋሪ እንዲሆን የክልል አፈ-ጉባዔዎችን ጨምሮ ስፖርትን የሚመሩ የቢሮ ኃላፊዎች ረቂቅ ዐዋጁን አስመልክቶ የተለያዩ ሐሳቦችን በማሰባሰብ ለረቂቅ ዐዋጁ መዳበር አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ ይገባል ብለዋል።



*በፌዴራል የስፖርት ልማት እና አሥተዳደር ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ ከተካሄዱ የአስረጂ መድረኮች መካከል አንዱ፤*

በወሩ የተካሄደው ኹለተኛው የአስረጂ መድረክ፣ **የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዐዋጅን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ ሲሆን፣ የአስረጂ መድረኩን የመራው በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑም ተጠቅሷል። በዚኹ የአስረጂ መድረክ ላይ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፣ የቋሚ ኮሚቴው አባላት እና በግብርና ሚኒስቴር የግብዓት እና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታዋ ዶ.ር. ሶፊያ ካሣ እና የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነርን ጨምሮ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተው ነበር ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ሰለሞን ላሌ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በትርፍ የሚመሩ፣ የሚያድጉ እና የአገር ኢኮኖሚን የሚያሸጋግሩ መሆን አለባቸው ብለዋል። ነባሩ ዐዋጅ ለ10 ዓመታት ያለ ደንብ የቆየ መሆኑን ያነሱት ሰብሳቢው፣ ዐዋጅ ያለ ደንብ ዐዋጅ አይሆንምና፣ አዲሱ ማሻሻያ ግን ይኽንን ክፍተት የሚደፍን እና ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው ማለታቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታዋ ሶፍያ ካሣ በበኩላቸው፣ አዲሱ ማሻሻያ ዐዋጅ በኢኮኖሚ እና በማኅበራዊ ዘርፍ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያም በዘርፉ ተጠቃሚ የምትሆንበትን ዕድል ይፈጥራል ሲሉ ተናግረዋል ተብሏል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌትነት ታደሠ በበኩላቸው፣ ይኽ ማሻሻያ ዐዋጅ መዳረሻችንን የምንለይበት እና በዘርፉ ተመሳሳይ ተግባቦት የምንፈጥርበት ነው በማለት ረቂቁ ያለውን ፋይዳ አስረድተዋል። ኮሚሽነሩ አክለውም አዲሱ ዐዋጅ ማኅበራት ውጤታማ የሚሆኑበትን እና ሚናቸውን ለይተው እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል ግልጽ አደረጃጀት የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታዋ የተከበሩ ወይዘሮ መሠረት ኃይሌ በበኩላቸው፣ የኅብረት ሥራ ዘርፉ መንግስት ከጀመረው የማሻሻያ ሥራዎች መካከል አንደኛው ዘርፍ መሆኑን ጠቅሰው፣ ማሻሻያውን የበለጠ ለማጠናከር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው ማስቻል ያስፈልጋል ብለዋል ተብሏል።



*በየኅብረት ሥራ ማኅበራት ዐዋጅን ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ የተካሄደው የአስረጂ መድረክ በከፊል፤*

የወርኃ የካቲቱ ሦሥተኛው የአስረጂ መድረክ፣ **የኢትዮጵያ የአቬዬሽን ሴኪዩሪቲ ረቂቅ ዐዋጅን** የተመለከተው ሲሆን፤ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይመለከታቸዋል ከተባሉት ባለ ድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ አካሂዷል።

በውይይቱም ከባለድርሻ አካላት ግልጽነት ያስፈልጋቸዋል የተባሉ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች ተነስተው በብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት የሥራ ኃላፊዎች ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል ተብሏል፡፡

የከተማ መሠረተ-ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ፕሮፌሰር መሀመድ አብዶ በሰጡት አስተያየትም፣ ረቂቅ ዐዋጁ በአቬዬሽን ደኅንነት ዘርፍ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ደረጃ ከፍ በማድረግ ረገድ ፋይዳው ከፍተኛ ስለሆነ ግልፅነት የጎደላቸውን ቃላት በማስተካከል ጸድቆ ወደ ተግባር እንዲገባ ጥረት መደረግ አለበት ብለዋል፡፡

የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈተሀ መሀዲ በበኩላቸው፣ ዐዋጁ በጥራቱ እና በቅልጥፍናው የአቬዬሽን ደኅንነትን የበለጠ የሚያጠናክር እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓለም ዓቀፍ የአቬዬሽን ደኅንነት መመዘኛን በማሟላት ቀዳሚ ሆኖ እንዲቀጥል ያስችላል ብለዋል፡፡ የብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሲሳይ ቶላ በበኩላቸው፣ በአየር ትራንስፖርት ሥርዓቱ የሚቃጡ የሕገ-ወጥ ድርጊቶች ባህሪያት እና የአፈፃፀም ስልት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየተወሳሰበ በመምጣቱ የአቭዬሽን ደኅንነት ስጋቶችን በብቃት መከላከል እንዲያስችል ቀደም ሲል የነበረው የአቭዬሽን ሴኩዩሪቲ ዐዋጅ ቁጥር 432/1997ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል ተብሏል።



*በአቬዬሽን ሴክዩሪቲ ረቂቅ ዐዋጅን የተመለከተው የአስረጂ መድረክ በከፊል፤*

## 2. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው የዓመቱ ስድስተኛ ወር፣ የኢትዮጵያ አንደራሴዎች የአምስት የፌደራል ተቋማትን የበጀት ዓመቱን ከመንፈቅ የሥራ አፈጻጸም፣ የየተቋማቱን የሥራ ኀላፊዎች ወደ አደራሻቸው ጠርተው አድምጠዋል፤ አሉ ያሏቸውን አስተያየቶች እና ጥያቄዎችን አንስተው ማብራሪያዎቹን ሰምተዋል።

### የተቋማት ሪፖርቶች

የኢትዮጵያ አንደራሴዎች በወርኃ የካቲትም የተለያዩ ፌደራላዊ ተቋማትን ወደ ምክር ቤታቸው ጠርተው፣ ተቋማዊ ሪፓርታቸውን እንዲያቀርቡ አድርገዋል። ከእነዚኽ የወሩ ተረኛ ሪፖርት አቅራቢ ከነበሩት መካከል በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚው የነበረው **የግብርና ሚኒስቴር** ሲሆን፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም የዚኽን በጀት ዓመት የመንፈቅ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት፣ በአንደራሴዎቹ ምክር ቤት ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰለሞን ላሌ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ከነበሩበት ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ተላቆ ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ በተደረገው ጥረት በኹሉም መስኮች አስደማሚ ስኬቶችን ማስመዝገብ እንደቻለ ገልጸዋል። በአርሶ እና በአርብቶ አደሩ የተጀመሩ ሥራዎች የተጀመረውን የግብርና ሽግግር እቅድ ከግብ ለማድረስ እንደሚቻል ማሳያዎች ናቸው ያሉት ሰብሳቢው፣ በግብርናው ዘርፍ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብና እና የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ለማድረግ በጊዜ የለኝም መንፈስ በትጋት መሥራት እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል ተብሏል።

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ክቡር አዲሱ አረጋ በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያን ግብርና ሽግግር እቅድ ግቡን እንዲመታ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በግብርናው ዘርፍ በ2018 በጀት ዓመት 6 ወራት ውስጥ በኹሉም ዘርፎች ከእቅድ በላይ መከናወኑን ተናግረዋል። ምርት እና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፣ የአፈር አሲዳማነትን ለመከላከል የ15 ዓመት ፕሮግራም ተይዞ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል ተብሏል።

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታዋ ዶ.ር. ሶፊያ ካሣ በበኩላቸው፣ የበጀት ዓመቱ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት በመጠንም ሆነ በስርጭት ከባለፈው ዓመት የተሻለ መሆኑን ገልጸው፣ በወቅቱ ለአርሶ አደሩ እንዲደርስ በትኩረት እየተሰራ መሆኑንም መግለጻቸውን ዘገባው ያሳያል።



***የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትሩ አዲሱ አረጋ የበጀት ዓመት የመንፈቁን ሪፖርት ሲያቅርቡ፤***

የወሩ ኹለተኛ የበጀት ዓመቱ ግማሽ ዓመት ሪፖርት አቅራቢ የነበሩት **የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ኤሌክትሪክ ኃይል** ሲሆኑ፣ የተቋሙን ሪፖርት ያደመጠው ደግሞ፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተጠቅሷል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ የተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን በማዘመን ለኅብረተሰቡ ምቹ እና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አያይዘውም፣ ከለውጡ በኋላ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ከነበረባቸው ውስብስብ ችግሮች ወጥተው ትርፋማ እየሆኑ መምጣታቸውን ገልጸዋል። በኹለቱ ተቋማት መካከል የለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር ለኅብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት አጠናክሮ መሥራት ይገባል ሲሉም ሰብሳቢው አክለው መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ሰለሺ ኮሬ በበኩላቸው፣ በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በቀጣይነት በምክር ቤቱ ለተቋማቱ የተሻለ በጀት ሊመደብላቸው እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አሥፈጻሚው ኢንጂነር ጌቱ ገረመው በበኩላቸው፣ እንደራሴዎቹ በ2017 ዓ.ም. በነበራቸው የውክልና ሥራ ወቅት ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ተቋሙ ኅብረተሰቡ ካነሳቸው እና እንደራሴዎቹ ለተቋሙ ካቀረቧቸው ጥያቄዎች መሀከል ሠላሣ አንድ በመቶ ለሚሆኑት ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት መቻሉን አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ኢንጂነር አሸብር ባልቻ በተራቸው፣ ባለፉት ስድስት ወራት ለጎረቤት አገራት በተደረገው የኢነርጂ ሽያጭ 67.3 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን መጥቀሳቸውን ዘገባው ጠቅሷቸዋል።



***የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት እና ኤሌክትሪክ ኃይል የግማሽ ዓመት ሪፖርትን ሲገመግም፤***

**የኢትዮጵያ የዕዳ እና ሀብት አሥተዳደር ኮርፖሬሽን፣** የ2018 በጀት ዓመት የስድስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸሙን፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ለየመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበበት ኹነት ደግሞ፣ የወሩ ሦሥተኛ የእንደራሴዎቹ የተቋማት ቁጥጥር ክንውን ነበር።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ የኮርፖሬሽኑን አሰራር እና አደረጃጀት በፍጥነት በማጠናከር እና የአገርን ሀብት በአግባቡ በማስተዳደር ዜጎችን በሚጠቅም መንገድ ሊሰራ እንደሚገባ አሳስበዋል። ሰብሳቢው አክለውም፣ አገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ተከትሎ የግል ይዞታ እና የመዋዕለ-ንዋይ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሆኑ ሕጋዊ የማድረግ ጉዳይ ተጠናክሮ ሊሰራ እንደሚገባም ገልጸዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ሰለሺ ኮሬም፣ ከዐብይ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ጋር ተያይዞ አብዛኛዎቹ የልማት ድርጅቶች ውጤታማ እና ትርፋማ እንዲሆኑ የተደረገው ጥረት አበረታች መሆኑን አንስተው፣ በኮርፖሬሽኑም የሌሎች አገራትን ተሞክሮ

በመውሰድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ማምጣት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የኮርፖሬሽኑ የቦርድ ሰብሳቢ እና የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታዋ ስመሪታ ሰዋስው በበኩላቸው፣ እንደ አገር የቆዩ የኢኮኖሚ ስብራቶችን ለመጠገን በርካታ ሥራዎች መሥራታቸውን ገልፀዋል። ሚኒስትር ዴኤታዋ አክለውም፣ የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል የማዞር ሥራዎች አሥተዳደር በታሰበው ልክ እንዳልተፈፀመ ገልፀው፣ መሠረታዊ እስትራቴጂክ ውሳኔ በማስፈለጉ ውሳኔው በአጠረ ጊዜ ለቋሚ ኮሚቴው እንደሚደርስ ተናግረዋል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ሙሉዓለም ጌታሁን በበኩላቸው፣ የዕዳ እና ሀብት ኮርፖሬሽን የመንግሥትን ዕዳ እና ሀብት ለማሥተዳደር እንዲችል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ያስቆጠረ መሆኑን አስታውሰው፣ በቋሚ ኮሚቴው የተሰጡ ግብረ-መልሶች ግን ተጠናክረው እንደሚፈፀሙ አስረድተዋል ተብሏል።



***የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ መለስ መና በሪፖርቱ ግምገማ ወቅት፤***

የወርኃ የካቲት ዐራተኛ ሪፖርት አቅራቢ ሆኖ የተሰየመው **የኢትዮጵያ አየር መንገድ** ሲሆን፣ የተቋሙን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም ያቀረቡት ደግሞ፣ ዋና ሥራ አሥፈፃሚው መስፍን ጣሰው ነበሩ።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ መለሠ መናም፣ ተቋሙ ለአገራችን የውጭ ምንዛሬን ከማስገኘት አኳያ ትልቅ ድርሻ ያለው በመሆኑ ይህንን ውጤት በማስጠበቅ እየፈፀመ ያለው ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አሳስበዋል። ሰብሳቢው አክለውም፣ አየር መንገዱ በየዕለቱ ተለዋዋጭ በሆነ ዓለም ውስጥ ለሚፈጠሩ ችግሮች መፍትሔ በመስጠት እና ከፍታውን ለማስጠበቅ የአገር ውስጥ እና ዓለም ዓቀፍ የበረራ መዳረሻዎችን ከማስፋት እንዲሁም በነበሩ መዳረሻዎች ላይ የበረራ ድግግሞሽን በመጨመር የማይዋዥቅ ሥርዓትን ተግባራዊ እያደረገ መጓዙ የሚበረታታ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ 6ስድስት ወራት አፈፃፀም የላቀ ቢሆንም በተለይ አየር መንገዱ የጀመራቸው የቢሾፍቱ ዓለም ዓቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታን ጨምሮ 28 ፕሮጀክቶች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ፣ የወጪ መጠን እና ጥራት ልክ ለማጠናቀቅ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊከታተል እንደሚገባም የተከበሩ መለስ መናገራቸው ተጠቁሟል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አሥፈፃሚ መስፍን ጣሰው በበኩላቸው አየር መንገዱ ደረጃውን አስጠብቆ ለመጓዝ የሚያስችሉ የተለያዩ ሥራዎችን በተጠናቀቀው ስድስት ወራት ማከናወኑን አንስተዋል። ከዚህም ውስጥ ባለፉት ስድስት ወራት 7 ተጨማሪ አውሮፕላኖችን አስመጥተው ወደ ሥራ ማስገባታቸውን እንዲሁም የአገር ውስጥ አውሮፕላን ማረፊያዎችን ከመጠገን ባለፈ ተጨማሪ 4 መዳረሻዎችን በመጨመር በተያዘው በጀት ዓመት የአገር ውስጥ በረራን ከ23 ወደ 27 ለማድረስ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።



*የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አሥፈፃሚው መስፍን ጣሰው፣ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

ዋና ሥራ አሥፈጻሚው አክለውም፣ በቢሾፍቱ እየተጀመረ ላለው ዓለም ዓቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ የቅድመ ዝግጅት ሥራ እየተጠናቀቀ እና በቅርቡም የግንባታ ሥራው በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት እንደሚጀመር አስረድተዋል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወሩ ባካሄደው 5ኛ ዓመት 1ኛ አስቸኳይ ስብሰባው **የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን** የዐራት ዓመታት ሪፖርትም ገምግሟል። ምክር ቤቱ በአስቸኳይ ስብሰባው የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከተቋቋመበት የካተት 2014 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ አሁን ያከናወናቸውን ተግባራት እና ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት፣ በኮሚሽኑ ኮሚሽነር ፕ/ር መስፍን አርአያ ቀርቦለት ነበር ተብሏል።

በዚኹ ስብሰባ ላይ፣ እንደራሴዎቹ በሪፖርቱ ዙሪያ ሰፊ ውይይት ማድረጋቸው ሲዘገብ፤ በተለይም የምክክር ሂደቱ የትግራይ ክልልን ጨምሮ ኹሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ከማሳተፍ፣ በግጭት ቀጠናዎች ካለው ተደራሽነት አንጻር፣ ለአጀንዳዎች የተሰጠው ጊዜ በቂ መሆን ብሎም ጥንካሬዎች እና ድክመቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ ጥያቄዎችን አንስተዋል።

ዋና ኮሚሽነሩ ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ባለፉት ዐራት ዓመታት በአገር ውስጥ እና በውጭ የተካሄዱ የአጀንዳ ማሰባሰብ እና የተሳታፊ ልየታ ተግባራትን በዝርዝር አቅርበዋል። በምክር ቤቱ የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ እውነቱ አለነ፣ ኮሚሽኑ ባለፉት ዓመታት ለቀጣይ የምክክር ሂደቱ ተግባራት ወሳኝ መሰረት የሚጥሉ ሥራዎችን ማከናወኑን መጥቀሳቸውም ተዘግቧል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጀጌ በበኩላቸው፣ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በአገረ-መንግሥት ግንባታ ውስጥ በየዘመኑ የተሻገሩ ስብራቶችን ለመጠገን ጉልህ ሚና ይጫወታል ሲሉ ገልጸዋል። ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ እንደገለፁት፣ መንግስት ለዘመናት በሩ የተዘጋበትን ጥያቄ ወደ መድረክ በማምጣት ኢትዮጵያውያን በችግሮቻቸው ዙሪያ እንዲመክሩ እና በየዘመናቱ የሚፈራረቁ ግጭቶችን ለመፍታት የምክክር መድረክ በማመቻቸት አገራዊ ምክክር ኮሚሽን እንዲኖር ይህን ተቋም መፍጠሩ እንደ አገር ትልቅ ምዕራፍ እንዲከፈት ታሪካዊ ሥራ መሥራቱንም ተናግረዋል ተብሏል።

ኮሚሽኑ ባለፉት ዐራት አመታት ልሂቃንን ብቻ ሳይሆን ኹሉንም የአገሪቱ ዜጋ ባሳተፈ መልኩ ምክክር በማድረግ ግቡን በሚያሳካ ኹኔታ በርካታ ሥራዎች መሥራቱን እና በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በሒደቱ መሳተፋቸውን ያነሱት ዶ.ር. ተስፋዬ፣ በትግራይ ክልልም እንደ ሌሎች ክልሎች ኹሉ የአገራዊ ምክክር ሂደቶች እና መድረኮች መካሄዳቸውን አንስተዋል።

በመድረኮቹም የሲቪል ማኅበረሰቡ ወኪሎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣

ጊዜያዊ አሥተዳደሩ በምክክር ሒደቱ መሳተፋቸውን ገልፀዋል ተብሏል። አገራዊ ምክክሩ ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ተሸጋግሯል ሲሉ የተደመጡት ደግሞ፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሠ ጫፎ ሲሆኑ፤ ኮሚሽኑ እስከአኹን ያከናወናቸው ተግባራት አገራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችል ጠንካራ መሠረት የጣለ መሆኑን አስገነዘበዋል። በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት አጀንዳ በማሰባሰብ እና ተሳታፊዎችን በመለየት ረገድ ሰፊ ሥራዎችን ኮሚሽኑ ማከናወኑን ያነሱት አፈ-ጉባኤው፣ በትግራይ ክልልም ቢሆን ሥራዎች አልተሠሩም ማለት አይቻልም፤ በክልሉ ተካሄዱ 22 የውይይት መድረኮች ዋና ዋና ጉዳዮች ተለይተዋል ሲሉ መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል። አፈ-ጉባኤው አክለውም የትግራይ ክልል ጉዳይ የጋራችን ነው፤ በቀጣይ አጀንዳ የመረከብ እና ተሳታፊ የመለየት ሥራው በጥንቃቄ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ባቀረቡት ዝርዝር ሪፖርት፣ ባለፉት 4 ዓመታት 93 በመቶ በሚሆኑ ወረዳዎች አጀንዳዎች መሰብሰባቸውን እና ከ126 ሺሕ በላይ ተሳታፊዎች መለየታቸውን ገልጸዋል። በተለይም በአማራ ክልል ትጥቅ የታጣቀ ቡድን ትጥቅ ፈትቶ ወደ ሠላማዊ መንገድ መምጣት መቻሉ እና አጀንዳዎቹን ማስረከቡ ለሒደቱ ትልቅ ስኬት መሆኑን ጠቅሰዋል ተብሏል። የምክክር ኮሚሽኑ የተጨመረለትን የ1 ዓመት ጊዜ የካቲት 14/2018 የሚያጠናቅቅ በመሆኑ ቀሪ ሥራዎቹን የሚያከናውንበት ከየካቲት 15 ጀምሮ የሚቆጠር የ8 ወራት ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው የውሳኔ ሐሳብ ቀርቦ፣ ሐሳቡም ቁጥር 8/2018 ሆኖ በሙሉ ድምፅ ፀድቋል። በዚኽ የምክክር ኮሚሽኑ አጠቃላይ ተቋማዊ ኹኔታ፣ የኢትዮጵያ ትምክር ሂደት እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዮች የተዘጋጀውን የብሪፎ ዳሰሳዊ ምልከታ በገጽ 27 ይመለከቷል።



*የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነሩ ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ፣ በሪፖርታቸው ወቅት፤*

## የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የኤፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች አባላት፣ በውሩ ውስጥ ምንም ዓይነት የተቋማት ጉብኝቶችን ባያደርጉም ቅሉ፣ የተወሰኑ የመስክ ምልከታዎችን ማካሄዳቸውን እንደራሴ ያሰባሰባቻቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## የመስክ ጉብኝቶች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ የካቲትም የተወሰኑ የመስክ ጉብኝቶችን ከውነው ነበር። በጊዜ ምጣኔ በቀዳሚነት የመስክ ምልከታ የተካሄደባት **ኦሮሚያ** ስትሆን፣ ወደዚያች ክልል የደረሰውም በምክር ቤቱ **የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ** ነበር ተብሏል። ቱሪዝም ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ እና የአገር ገፅታን ለመገንባት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው በምልከታው ወቅት የጠቀሰው ቋሚ ኮሚቴውም፣ በክልሉ ያሉትን የቱሪስት መስህቦች በማስተዋወቅ ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ጎብኚዎች ምቹ ኹኔታን በመፍጠር ረገድ

የቱሪስት መሠረተ ልማቱ ላይ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ አስገንዝባል ተብሏል። ቋሚ ኮሚቴው በክልሉ ካያቸው የቱሪስት መስህቦች መካከል፣ **የጅማ አባጅፋር ቤተ-መንግሥት፣ በቡኖ በደሌ እና በኢሊባቡር ዞኖች የሚገኙት ደንገዋጂ እና ሶር ፏፏቴዎች** ይገኙበታል ተብሏል።



***የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት በኦሮሚያ የመስክ ምልከታቸው ወቅት፤***

በዚኹ ወር፣ **በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የሚገኘው ምሥራቅ ጉራጌ ዞንም፣** የመስክ ጉብኝት እንደተካሄደበት ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ያሳያል። በዞኑ ወደምትገኘው **ቡታጅራ ከተማ** የተጓዙት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት **የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ** ሰብሳቢዋ እና የሶዶ ምርጫ ክልል እንደራሴዋ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግስቱ ሲሆኑ፤ እርሳቸውም፣ ባለፉት ጊዜያት ከመራጩ ሕዝብ ጋር በነበሩ ውይይቶች የተነሱ የልማት እና መልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት ጋር በቅንጅት በመሥራት ውጤት ማምጣት ተችሏል ብለዋል።

ለዚህም ኬላ-ቱሉ-ቦሌ-አስፓልት መንገድ ትልቅ ማሳያ ነው ያሉት የተከበሩ እፀገነት፣ መንገዱ በጊዜ ባለመጠናቀቁ ከፍተኛ የሕዝብ ቅሬታ ይነሳበት የነበረ ሲሆን፣ በተደረጉ ጥረቶች ተግዳሮቶችን በመፍታት በአጭር ጊዜ ተጠናቆ ለአገልግሎት እንዲበቃ መደረጉን ተናግረዋል ሲል ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።

ሌላይኛዋ እንደራሴ እና የመስቃን ቁጥር አንድ ምርጫ ክልል ተወካይ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቅነሽ ጀማል በበኩላቸው፣ በቡታጅራ ከተማ እየተሰሩ ያሉ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ተግባራት የማኅበረሰቡን ተጠቃሚነት እያረጋገጡ የሚገኙ በመሆናቸው ተጠናክረው መቀጠል እንደሚገባቸው ገልጸዋል ተብሏል።

የምሥራቅ ጉራጌ ዞን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ አቶ እንዳልካቸው ጌታቸው በተራቸው፣ በቡታጅራ ከተማ ብሎም በአጠቃላይ በዞኑ እየተከናወኑ የሚገኙ የልማት ፕሮጀክቶች አበረታች መሆናቸውን ገልፀው፣ ለበለጠ ውጤት እና ስኬት ኹሉም ባለድርሻ አካል የበኩሉን ሊወጣ ይገባል ማለታቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል።



***በምሥራቅ ጉራጌ ዞን የተካሄደው የመስክ ምልከታው በከፊል፤***

## 3. የውክልና ሥራች

በመግቢያችን እንደጠቀስነው ወሩ የውክልና ሥራ የሚከውንበት እንደመሆኑ፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ካሉባቸው ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነቶች መካከል አንዱ የሆነውን ይኸው የውክልና ሥራቸውን ሰፋ አድርገው አከናውነዋል። በዚኽም፣ የምክር ቤቱን ምክትል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶን ጨምሮ ከስድሳ የማያንሱ እንደራሴዎች ወደ'ምርጫ ክልሎቻቸው በመሄድ ከመራጮቻቸው ጋር፣ በአገራዊ እና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ሲመክሩ ሰንብተዋል።

ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ 11፣ሲዳማ 3፣ ኦሮሚያ 19፣ ሱማሌ 1 ፣ አማራ 6 ፣ አዲስ አበባ 5 ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ 11 ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ 1 እንዲኹም አፋር ክልል ደግሞ 1 እንደራሴያቸውን ልከው የመራጭ-ተመራጭ መድረክ ማካሄዳቸውን እንደራሴ ከምክር ቤቱ ያሰባሰበቻቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ።

### የማዕከላዊ ኢትዮጵያ መራጮች ምን ጉዳዮች አሳሰቡን አሉ?

በወርኃ የካቲት እንደራሴዎቹ ሕገ-መንግሥታዊ የውክልና ኀላፊነታቸውን ካከናወኑባቸው ክልሎች በዛ ያሉ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች የተካሄዱት በአዲሷ የፌዴሬሽኗ ክልል **ማዕከላዊ ኢትዮጵያ** ነበር።

አስቀድመው በክልሉ ወደሚገኘው **ሀዲያ ዞን ኮንተብ 03 ምርጫ ክልል** የደረሱት እንደራሴዋ **የተከበሩ ወ/ሮ ሙሉነሽ ላሞሬ፣** ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሕዝብ ተወካዮች እንዲሁም ከወረዳው አመራር እና ከሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች ከተወጣጡ ተወካዮች ጋር ተወያይተዋል ተብሏል።

በምርጫ ዘመኑ ሲጠየቁ ከነበሩ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥቄዎች ምላሽ የተሠጠ መሆኑን በመራጭ ተመራጭ መድረኩ ላይ ያነሱት እንደራሴዋ ወ/ሮ ሙሉነሽ፣ ምላሽ ከተሰጠባቸው ጥያቄዎች መካከልም ከአፈር ማደበሪያ እስከ የእንስሳት ህክምና፣ ከመንገድ ጥገናዎች እስከ ከተማ እና መሠረተ ልማት፣ ከሥራ እድል ፈጠራ እስከ የኮርደር ልማት ያሉትን ለአብነት አንስተዋል ተብሏል፡፡

ወደዚኹ ክልል ወደሚገኘው **ሀዲያ ዞን በሾኔ ከተማ አሥተዳደር በሲቄ 02 ምርጫ ክልል** የተጓዙት ሌላይኛዋ እንደራሴ **የተከበሩ ወ/ሮ ነቢያት ጥላሁን፣** የውክልና ሥራን አስመልክቶ ባቀረቡት ሪፖርት፣ መራጮች በተለያዩ ጊዜያት የሚያነሷቸው የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች በየደረጃው እንዲፈታ እና የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎች ውጤት እንዲያመጡ በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እንዲሁም በመናበብ ከፍተኛ ጥረት የተደረገበት እና ምላሽ ያገኙም ጥያቄዎች እንዳሉ ገልፀዋል ተብሏል።

በዚኹ ክልል ወደሚገኘው ሌላይኛው ዞን ወደሆነው **ጉራጌ ዞን ገደባኖ ጉታዘር ወለኔ ወረዳ** የተጓዙት በጉራጌ ዞን **የተከበሩ ወ/ሮ ሳድያ ተማም** ሲሆኑ፣ 'ርሳቸውም ከመራጮቻቸው በዛ ያሉ አስተያየቶችን እና ጥያቄዎችን አድምጠዋል።

ተወያዮቹም፣ ባለፉት ዓመታት የብልጽግና መንግስት የኅብረተሰቡን የልማት እና የመልካም አሥተዳደር

ጥያቄዎችን ለመመለስ ሕዝቡን ተጠቃሚ ያደረጉ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ማከናወኑን ጠቅሠው፣ በዚኽም በአካባቢያቸው የለውጡ ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል ተብሏል፡፡

ወደ በምሥራቅ ጉራጌ ዞን ሶዶ ምርጫ ክልል የሄዱት ደግሞ፣ በምክር ቤቱ **የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግስቱ** ሲሆኑ፣ በአካባቢው የሕዝብን የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ችግሮችን መፍታት የሚያስችሉ በርካታ ፕሮጀክቶች መሠራታቸውን እና እየተሰሩም እንደሚገኙ ከመራጮቻቸው ተረድተዋል ተብሏል፡፡

በዚኹ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ወደሚገኘው ጠምባሮ ምርጫ ክልል ብቅ ያሉት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት **የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃ** በበኩላቸው፣ በምርጫ ክልሉ በርካታ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳ ያላቸው ልማቶች እየተሰሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል ሲል ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷቸዋል፡፡

በዚኹ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በሚገኘው **ዌራ ወረዳ ሙዱ-ዲኖቆሳ ወረዳ** ከተወጣጡ የማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር የመራጭ-ተመራጭ መድረክ ያካሄዱት ደግሞ **የተከበሩ ዶ.ር. ነጃት ግርማ** ሲሆኑ፤ በመድረኩ ያገኟቸው ተወያዮችም፣ ከለውጡ መንግስት በኋላ በርካታ የመሠረተ ልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች በተሻለ መልኩ እየተፈቱ መሆናቸውን ገልፀውላቸዋል ተብሏል፡፡



***በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከተካሄዱ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች መካከል፤***

የተከበሩ ነጃት ግርማ በበኩላቸው፣ የሕዝቡን ችግር ለመቅረፍ መንግስት የረጅም እና የአጭር ጊዜ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ቀርጾ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቅሰው፤ እንደአገር ካሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮች አንፃር በሕዝብ ፍላጎት ልክ ምላሾች ለመስጠት የተቸገረ ቢሆንም መንግስት በተቻለ አቅም ችግሩን በየደረጃው ለመፍታት እየሰራ መሆኑን ለተወያዮቹ ነግረዋቸዋል፡፡

እኚሁ እንደራሴም፣ ወደ ሀላባ ዞን በዌራ ዲጆ ወረዳም ተጉዘው ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በልማት እና መልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ላይ ውይይት ማካሄዳቸው ሲዘገብ፤ እርሳቸውም የለውጡ መንግስት ለሕዝቡ የገባውን ቃል እየፈጸመ፣ ከሕዝብ የሚነሱ የመሠረተ ልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎችን እልባት እንዲያገኙ በትኩረት እየሰራ መሆኑንም ማስገንዘባቸው ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቁሟል፡፡

ሌላኛዋ እንደራሴ እና በዚያው መድረክ የተገኙት **የተከበሩ ወ/ሮ መነቴ ሙንዲኖ** በበኩላቸው፣ ተወካዮች ከሕዝቡ የተነሱ የመሠረተ ልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች እልባት እንዲያገኙ ጠንካራ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በመራጮቹ የተነሱ ጥያቄዎች ደረጃ በደረጃ እንዲፈቱ ከሚመለከታቸው

የመንግስት አካላት ጋር ጥልቅ ውይይት የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት **የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁም፣** በዚኹ ወር ወደዚኹ ክልል ከሄዱት እንደራሴዎች መካከል አንዱ ነበሩ። **በሀዲያ ዞን በምሥራቅ ባደዋቾ ወረዳ በሲቄ 01 እና 02 ምርጫ ክልል** ላይ የመራጭ-ተመራጭ ውይይቱን የመሩት እንደራሴውም፣ ከኅብረተሰቡ የተነሱ ጥያቄዎች በየደረጃው ላለው መዋቅር እንደሚቀርብ እና ክትትል እንደሚደርግ ጠቅሰው፤ ኅብረተሰቡ ሰባተኛው አገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ነፃ፣ ፍትሓዊ እና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ መልዕክት አስተላልፈዋል ተብሏል።

**በዳሎቻ ምርጫ ክልልም** እንዲኹ በእንደራሴዋ **የተከበሩ አበባ ሳዲቅህ** አማካኝነት በየተካሄደው የውክልና መድረክ፣ በልማት እና በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት መካሄዱ ሲዘገብ፤ ቀደም ሲል በህብረተሰቡ ዘንድ የተነሱ ጥያቄዎች ላይ መልካም ምላሽ መሠጠቱን የጠቀሱት እንደራሴዋ፣ በቀጣይም በፕሮጀክቶች አፈጻጸም መሻሻል እንዲደረግ፣ በመንገድ እና በመስኖ ፕሮጀክቶች ካሳ ላልተከፈላቸው ተነሺ አርሶ አደሮች ካሳ እንዲከፈል እና ከፍተኛ የውኃ ችግር ላለባቸው ቀበሌዎች ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡

**የተከበሩ ዶ.ር. ቤዛ ተሾመም፣ በአንጋጫ ከተማ** አሥተዳደር ከሚገኙ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር መወያየታቸው ሲጠቀስ፣ ውይይቱም ከስድስተኛው ዙር ምርጫ ወዲኽ በመንግሥት የተሰሩ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ የልማት ሥራዎች እና በ 2017 ዓ.ም. የክረምት የሕዝብ ውክልና ሥራ ወቅት በሕዝብ የተጠየቁ ጥያቄዎች ያሉበትን ደረጃ በተመለከተ ሰፋ ያለ መድረክ ነበር ተብሏል።

## ከሲዳማ የተሰማው

በዚኽ የእንደራሴዎቹ ሕገ-መንግሥታዊ የውክልና ሥራ በወሩ ከተጎበኙት ክልሎች ሌላኛዋ ሲዳማ ስትሆን፣ የተወሰኑ የክልሉ የምርጫ ወረዳዎች የመራጭ-ተመራጭ ውይይቶችን አስተናግደዋል። **በማዕከላዊ ሲዳማ ዞን በዱባ ምርጫ ክልል በዳሌ ወረዳ በዋይጨና ዳጋራ ቀበሌ ክላስተር** እንዲኹም **ቦአበደገሎ ቀበሌ** በነበረው የመራጭ-ተመራጭ መድረክ፣ እንደራሴዎቹ **የተከበሩ ሰለሞን ላሌ እና የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ማሞ** በተገኙበት ውይይት የተደረገ ሲሆን፣ በውይይቱ የተሳተፉ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት አባቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች እና የመንግስት ሠራተኞች ከስድስተኛው ዙር ምርጫ ወዲህ ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው ባለው የመንግስት መዋቅር በርካታ ሥራዎች መሠራታቸው ገልጸዋል ተብሏል።

ወደዚኹ ክልል **ደቡባዊ ሲዳማ ዞን ዳራ ምርጫ ክልል** የደረሱት **የተከበሩ ወይዘሮ አለሚቱ አበበ** በበኩላቸው፣ ከኅብረተሰቡ ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እና ማብራሪያ ከሰጡ በኋላ፣ በቀጣይም ትኩረት እንዲሰጥ በሚል የተነሱ ጉዳዮች በየደረጃው ላለው መዋቅር የሚቀርቡ መሆናቸውን እና አፈጻጸማቸውንም እንደሚከታተሉ መግለጻቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*የተከበሩ ሰለሞን ላሌ እና የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ማሞ፣ በመራጭ-ተመራጭ መድረኩ ወቅት፤*

## ከኦሮሚያስ...

በኦሮሚያ ክልል በተካሄደው የውክልና ሥራ፣ ወደ **ጅማ ዞን ሰኮሩ ምርጫ ክልል** ያቀኑት **የተከበሩ ፈይድ ሽራብ**፣ መንግስት ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት እንድትሆን እያደረገች ያለውን ጥረት አብራርተው፣ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በተገኘው ውጤት ሕዝቡ ተጠቃሚ እየሆነ መምጣቱንም ገልጸዋል ተብሏል።

በዚያው ጅማ ዞን ለዚኹ ግብር ብቅ ያሉት **የተከበሩ አቶ ሞጋ አባቡልጉም**፣ 7ተኛው አገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና አሳታፊ እንዲሆን መሥራት በሚሉ አጀንዳዎች ዙሪያ ኅብረተሰቡን አወያይተዋል።

ወደዚኹ ዞን የተጓዙት ሌላይኛው እንደራሴ የተከበሩ **ዶ.ር. ኑራዚማን ጅብሪል፣** ባለፉት አምስት ዓመታት የተከናወኑ ሥራዎች እና የተመለሱ የሕዝብ ጥያቄዎች እንዳሉ ሁሉ፣ የመንገድ፣ የመብራት ተደራሽነት፣ የኑሮ ውድነት እና ትምህርትን የመሳሰሉት መሠረተ-ልማቶች በቀጣይ ትኩረት ተደርጎባቸው እንደሚሠሩ መጥቀሳቸው ተዘግቧል።

ወደ **ምስራቅ ሸዋ ዞን ቦሰት ወረዳ ኦለንጪተ ምርጫ ክልል** የደረሱት **የተከበሩ ሹሚ አያኖ** በበኩላቸው፣ እርሳቸው የመሩት የመራጭ-ተመራጭ መድረክ፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተገኙበት እና በልማት፣ በሰላም እና ፀጥታ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ እና ለወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራ ላይ ያተኮረ እንደነበር መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት **የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ፕ/ር ሙሐመድ አብዶም፣ በባሌ ዞን ደሎ መና ምርጫ ጣቢያ** ስር በሚገኙ ወረዳዎች ከሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር መወያየታቸው ሲዘገብ፤ እንደራሴውም፣ በአገር ዓቀፍ ደረጃ የተከናወነው ዐብይ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ኢኮኖሚውን በማረጋጋት እና በውጪ ምንዛሬ ግኝት ላይ ያመጣውን ስኬት በዝርዝር ለተወያዮቻቸው አስረድተዋል ተብሏል።

በዚኹ **ኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን በአናሶራ ወረዳ በይርባ ሙዳ** እና አካባቢም የመራጭ-ተመራጭ ውይይት መካሄዱን ከእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ይኽንን የውክልና መድረክ የመሩት ደግሞ **የተከበሩ ዱቤ ጅሎ** ሲሆኑ፣ ‘ርሳቸውም ሕዝቡ በ7ኛው አገራዊ ምርጫ በንቃት እንዲሳተፍ እና ለዚኹም አስፈላጊውን ሂደት በማሟላት መመዝገብ ያለበት መሆኑን ጠቁመው፣ በምርጫው ዕለትም በነቂስ ወጥቶ ድምፁን መስጠት እንደሚገባው አስገንዝበዋል ተብሏል።

**በምዕራብ አርሲ ዞን ሻላ ወረዳ** በተካሄደው የመራጭ-ተመራጭ መድረክ ላይ የተገኙ መራጮች፣ በሰላም ኹኔታ፣ በልማት፣ በፕሮጀክቶች አፈጻጸም፣ በመልካም አሠተዳደር ችግሮች እና የአገልግሎት አሰጣጥ ጉድለቶች እንዲኹም በሥራ አጥነት ችግር ዙሪያ ያላቸውን ቅሬታ

በዚያ ለተገኙት የፌዴራል እና የክልል እንደራሴዎች እንስተውላቸዋል ተብሏል።

**በምዕራብ ሀረርጌ ዞን ጡሎ ወረዳ** የነበረውን የመራጮች መድረክ የመሩት **የተከበሩ ወ/ሮ አሻ ያህያ** በበኩላቸው፣ በባለፈው አራት ዓመት በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ መልካም አሥተዳደር እና በፀጥታ ጉዳዮች እንዲሁም በ7ኛው ዙር አገራዊ ምርጫ ዝግጅት ዙሪያ ውይይት እንደተካሄደ ገልጸዋል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት **ምክትል-አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶም፣ በምስራቅ ሸዋ ዞን ዱግዳ ወረዳ እና መቂ ከተማ** ተገኝተው ከወከሉት ማኅበረሰብ ጋር የመራጭ ተመራጭ ውይይት ማድረጋቸው ሲዘገብ፣ የአካባቢው ማኅበረሰብም ቀደም ሲል ከነበረበት የጸጥታ ስጋት ተላቆ የልማት ጥያቄዎችን ማቅረብ መጀመሩ እንዳስደሰታቸው ገልጸዋል ተብሏል።

ወደዚያው ዞን ለዚኹ ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነት የደረሱት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት **የከተማ እና መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. እሸቱ ተመስገን**፣ ከጨፌ ኦሮሚያ ምክር ቤት አባላት ጋር በመሆን የአከባቢውን ነዋሪዎች በሰላም፣ በልማት እና በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ላይ አወያይተዋል።

በዚኹ ዞን በሚገኘው **ቦቴ ከተማ** ከመራጮቻቸው ጋር የተወያዩት እንደራሴው **የተከበሩ ጫላ ለሚም፣** ሕዝብ የሚያነሳቸው እያንዳንዱ ጥያቄ ተገቢው ትኩረት የሚሰጠው እና እንደ መንግስት ምላሽ እየተሰጠው የሚሄድ መሆኑን ሲጠቅሱ፤ **ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን** የደረሱት **የተከበሩ ዶ.ር. ፍቃዱ መንግስቱ** በተራቸው፣ በወረዳው እና በአገር ዓቀፍ ደረጃ የተከናወኑ የልማት ሥራዎች ተስፋ ሰጪ እና እየተሻሻሉ መሆናቸውን ተናግረዋል ተብሏል።



*በየካቲት ወር በኦሮሚያ ከተካሄዱት የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች መካከል አንዱ፤*

ወደ አርሲ ሻገር ስንልም፣ **በምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ቁጥር 2 ምርጫ ክልል፣** በእንደራሴው **የተከበሩ ፕ/ር ቃሲም ኪሞ** መሪነት በተካሄደው የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ፣ በዋናነት በክረምት የሕዝብ ውክልና ጊዜ የተለዩ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች በእቅድ ተይዘው ምላሽ ያገኙትን ለመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ምክክር መደረጉ ሲዘገብ፤ ወደዚያው ያቀኑት **የተከበሩ ወ/ሮ ዜይናባ ኑራም፣** የኑሮ ውድነት፣ ግብርናን ማዘመን፣ የአረንጓዴ አሻራ ስራ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ፣ በየደረጃ ያሉት የፍትሕ አካላት አገልግሎት አሰጣጥ እና የባሕር ባር ጥያቄ የተወያዮቹ ዋንኛ አጀንዳዎች እንደነበሩ ተሰምቷል።

ወደ **ምዕራብ ሸዋ ዞን ከዳኖ ወረዳ እና ከሰዮ ከተማ** አሥተዳደር ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር የተወያዩት ደግሞ **የተከበሩ ዶ.ር. አለሙ ጎንፋ** መሆናቸው ሲጠቀስ፣ በዚያው ዞን ጉብኝት ያካሄዱት **የተከበሩ ወ/ሮ ነኢማ ዑስማንም**፣ ከመብራት እስከ ንጹሕ መጠጥ ውኃ እና ከትምህርት ጥራት እስከ የጤና መድን አገልግሎት

አሰጣጥና የደረሱ የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ከመራጮቻቸው በኩል ተነስተውላቸው ነበር ተብሏል።

**በምዕራብ አርሲ ዞን በነጌሌ አርሲ ከተማ** ከሚገኙት መራጮቻቸው ጋር የተወያዩት ደግሞ፣ **የተከበሩ ወ/ሮ ጀማይኔሽ ወ/ሚካኤል** እንደነበሩ ተጠቅሷል።

ከኦሮሚያ ከተሞች አንዷ በሆነችው **አዳማ ከተማ፣ የአዳማ 2 ምርጫ ክልል** የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ መካሄዱ ሲሰማ፣ መድረኩም የተመራው በእንደራሴዋ **የተከበሩ ወ/ሮ ኩመለ ገዲሰ** ሲሆን፤ በዚያችው ከተማ በሚገኘው **አዳማ 1 ምርጫ** ክልልም፣ **የተከበሩ ዶ/ር ተሾመ አብዶ** የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክ አካሂደዋል ተብሏል።

ወዲህ ወደ **ሞጆ ከተማ** ብቅ ስንልም እንዲኹ በወርኃ የካቲት የመራጭ-ተመራጭ ውይይት መካሄዱን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ያሳይል። ወደ ከተማዋ ብቅ ያሉት **የተከበሩ ወ/ሮ አዲስ አለማየሁ ቁምቢ**፣ ባለፉት አምስት ዓመታት በከተማው ነዋሪዎች በተደጋጋሚ ሲጠየቁ የነበሩ የመሠረተ ልማት ጥያቄዎች በፌዴራል መንግስት ተቋማት እና በከተማው መሥተዳድር ቅንጅት መልስ እንዲያገኙ መደረጉን ገልፀዋል ተብሏል።

## የሱማሌ ክልሉ መድረክ

በዓመቱ የመጀመሪያው ዙር በሆነው የእንደራሴዎቹ የውክልና ክንውን፣ ምሥራቃዊቷ የኢትዮጵያ ክልልም አንድ የመራጭ-ተመራጭ መድረክ አካሂዳለች ተብሏል። በዚኽ ብቸኛ መድረክም፣ በክልል በሚገኘው **ኦውበሬ ወረዳ** የሚገኙ ነዋሪዎች በሰላም፣ በልማት እና በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ፣ ከእንደራሴው **የተከበሩ ከማል ሃሺ ጋር** መክረዋል ተብሏል።



*የሱማሌው የመራጭ-ተመራጭ መድረክ በከፊል፤*

## ወደ አማራ ክልል. . .

በዚኽ ወርኃ የካቲት በተደረገው የመጀመሪያው ዙር የውክልና ሥራ፣ እንደራሴዎቹ ከሄዱባቸው ክልሎች ሌላይኛው አማራ ክልል ሲሆን፣ **በደቡብ ወሎ ዞን በተንታ ምርጫ ክልል** የፌዴራል እና የክልል የምክር ቤት አባላት ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በሰላም እና በመሠረተ ልማት ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አካሄደዋል። በውይይት መድረኩም **የተከበሩ ሀብተማርያም መኮንን** ሲገኙ፣ በውይይቱም ሁሉም ማኅበረሰብ ከመንግስት ጎን በመሆን ለሠላም ዘብ እንዲቆም እና 7ኛው አገራዊ ምርጫ ነፃ፣ ሰላማዊ እና ፍትሐዊ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ተወካዩ አስገንዝበዋል።

በዚያው አቅራቢያ **ደሴ ዙሪያ ወረዳ ቁጥር 1 ምርጫ ክልል** የደረሱት **የተከበሩ ራህመት አወል** በበኩላቸው፣ መንግስት እንደ አገር ከፍተኛ ልማቶችን በማስመዝገብ ሕዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑን መናገራቸው ሲዘገብ፤ እነማይ ወረዳ በብቸና ምርጫ ክልል ደግሞ፣ የተከበሩ አስቻለ አላምሬ በክልሉ አሁን እየተፈጠረ ያለውን የሠላም ችግር እንደምክንያት በመቁጠር በክልሉ በሸቀጦች ላይ ከፍተኛ የዋጋ ንረት

እየተፈጠረብን ይገኛል ሲሉ መራጮቻቸው እንደነገሯቸው ተዘግቧል።




*በአማራ ክልል ከተካሄዱት የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች መካከል አንዱ፤*

**ደቡብ ወሎ ዞን ለጋምቦ ወረዳ ምርጫ ክልል** የደረሱት **የተከበሩ አባተ አረጋ** በበኩላቸው፣ በምርጫ ዘመኑ መንግስት በብዙ ዓለም ዓቀፋዊ እና አገራዊ ፈተናዎች ውስጥ ቢገኝም፣ የብልፅግና ጉዞን የሚያሻግሩ ተግባራትን ማከናወኑን ለመራጮቻቸው ሲያስረዱ፤ **የተከበሩ ወ/ሮ ቅድስት አርአያም** እንዲኹ በላሊበላ ከተማ ተገኝተው ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር ውይይት አካሂደዋል ተብሏል። ወደ ማዕከላዊ ጎንደር ብቅ ላሉት የተከበሩ ተስፋሁን ስመኝም፣ የመንገድ ተደራሽነት፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎትና አቅርቦት እንዲኹም የንፁሕ መጠጥ ውኃ አቅርቦትን የመሳሰሉ የመሠረተ-ልማት ጥያቄዎች ከተወያዮቹ ተነስተውላቸው እንደነበር የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል።

## አዲስ አበባስ ምን አለች?

የፌዴሬሽኑ ዋና መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባም፣ በዚኹ ወርኃ የካቲት በተካሄደው የውክልና ሥራ ከተጎበኙ ከተማዎች መካከል ትገኝበታለች። በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በተካሄደው የመራጭ-ተመራጭ የፊት ለፊት ውይይት መድረክ፣ **የተከበሩ ዶ.ር. እንዳልካቸው ሌሊሳ፣** ያልተፈቱ ሥራዎች ቢኖሩም ባለፉት አምስት ዓመታት ግን ካቀድነው በላይ ሠርተናል ብለዋል ተብሏል። **በጉለሌ ክፍለ ከተማው** የመራጭ እና ተመራጭ የምክክር መድረክ ላይ የተገኙት **የተከበሩ ዶ/ር ቤተልሔም ላቀው** በበኩላቸው፣ ለክፍለ ከተማው ፈጣን እድገት እንደ ቁልፍ ሚና የሚጠቀሰው በሕግ አውጪው፣ በሕግ አሥፈጻሚው እና በሕግ ተርጓሚው መካከል ያለው የተቀናጀ አሰራር መሆኑን መናገራቸው ተጠቅሷል።

ልደታ ክፍለ ከተማ ብቅ ያሉት **የተከበሩ ወ/ሮ ሙሉ ይረጋም፣** ባለፉት ዓመታት ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በነበራቸው የመራጭ-ተመራጭ ውይይት ሲነሱ የነበሩ በርካታ ችግሮች በየጊዜው እየተፈቱ ተጨባጭ ለውጥ ተመዝግቧል ብለዋል።

ወደ **ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ** ስንሻገርም፣ **የተከበሩ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ** የመሩት እና 'ርሳቸውም፣ ሰላም ለማስፈን በአገር ዓቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ትኩረት እየተሰራ መሆኑን በማስታወስ፣ የሰላም ግንባታ ሥራን ከግብ ለማድረስ የሁሉም ማኅበረሰብ ክፍሎች ሚና ከፍተኛ መሆኑን መናራቸውን ተዘግቧል።

**የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው የተከበሩ ዶ.ር. ኬይረዲን ተዘራም፣** በ**ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ** ተገኝተው፣ ባለፉት ዓመታት ለሕዝብ ቃል የተገቡ እና በሕዝቡ መሠረታዊ ፍላጎቶች ላይ ያተኮሩ የመልካም አሥተዳደር ችግሮችን መፍታት እንደተቻለ ማብራራታቸውን ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ያሳያል።



*አዲስ አበባ ክፍለ-ከተሞች ከተካሄዱ የመራጭ-ተመራጭ መድረኮች መካከል፤*

## የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መራጮች ለእንደራሴዎቻቸው ምን አነሱላቸው?

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በሚገኘው **ጌዴኦ ዞን ዲላ ዙሪያ ወረዳ ሚችሌ ክላስተር** ከሚኖሩ መራጮቻቸው ጋር በመወያየት በጊዜ ምጣኔ ቀዳሚው የሆኑት **የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ፣** ከኅብረተሰቡ የተነሱ ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ደረጃ በደረጃ ምላሽ እንዲሰጡ ክትትል እንደሚደረግ ገልጸዋል ተብሏል።

ወደዚያው ዞን የተጓዙት **የተከበሩ ግዛቸው አየለም፣** በምክር ቤቱ እና በመንግስት ባለፉት አምስት ዓመት ከመንፈቅ በ6 ውስጥ የተሰሩ አንኳር ሥራዎችን ለመራጮቻቸው ማብራራታቸው ሲዘገብ፤ ወደ ኦፋ ምርጫ ክልል የተጓዙት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት **የመንግስት የልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ መለሰ መና፣** የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት የመረጣቸው ሕዝብ በሚያነሳቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በየ6 ወሩ እንደሚወያዩ ገልፀዋል ተናግረዋል ተብሏል።

**የተከበሩ አቶ ጋሻያለው ገላ** ደግሞ፣ በዚያው ክልል በሚገኘው **ጎፋ ዞን በዑባ ደብረ ፀሐይ ወረዳ እና በበቶ ከተማ አሥተዳደር** ካሉት መራጮቻቸው ጋር፣ በሰላም እና በጸጥታ ዙሪያ የሚነሱ ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታት ማኅበረሰቡ ከፀጥታ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት እንዳለበት አትኩሮት የተሰጠበትን የመራጭ-ተመራጭ መድረክ መርተዋል።

ወደዚያው ዞን **ላሃ ከተማ አሥተዳደር እና በመሎ ኮዛ ወረዳ አሥተዳደር** የደረሱት **የተከበሩ ወይዘሮ ትዕግሥት ታደለ** በበኩላቸው፣ 7ኛውን አገራዊ ምርጫ በስኬት ለማጠናቀቅ የሚያግዝ ውይይት አካሂጃለኹ ማለታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።




*በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከተካሄዱ የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረኮች መካከል፤*

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አንዱ ዞን በሆነው **ደቡብ ኦሞ ዞን** የተገኙት **የተከበሩ አጉ ደባን፣** በዳሰነች ወረዳ ከኦሞ ወንዝ ጋር ተያይዞ የፌደራል፣ የክልል እና የዞኑ አሥተዳደር ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ እንደሚገኙ ለመራጮቻቸው መናገራቸው ሲሰማ፤ **በአሪ ዞን ገሊላ ከተማ አሥተዳደር** ደግሞ፣ **በየተከበሩ ዶ.ር. ወልደየስ ደበበ** መሪነት፣ በልማት እና በመልካም አሥተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ የመራጭ-ተመራጭ መድረክ ተካሂዷል ተብሏል።

**በይርጋጨፌ ወረዳ በዲመርሶ ክላስተርም** እንዲኹ የመራጭ-ተመራጭ ውይይት መካሄዱ ሲዘገብ፤ መድረኩን የመሩትም **የተከበሩ ወ/ሮ ክብነሽ ሽፈራው** ነበሩ ተብሏል። **በወላይታ ዞን ዳሞት ፑላሳ ወረዳ እና ሻንቶ ከተማ አሥተዳደር** በተካሄደው እና **የተከበሩ ወ/ሮ እታፈራሁ ሞታ** በመሩት የመራጮች መድረክ፣ ለሕዝቡ ቃል ተገብቶላቸው ምላሽ ያገኙ እና እያገኙ ያሉ የልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጉዳዮችን የያዘ ሪፖርት በዝርዝር ለተወያዮቹ መቅረቡን የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት መረጃ ጠቅሷል።

ሕዝቡ 7ኛው አገራዊ ምርጫው ሠላማዊ፣ ፍትሐዊ እና በሕዝብ ዘንድ ቅቡልነት ያለው ሆኖ በሠላም እንዲጠናቀቅ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ መመጣት እንዳለበት ማስገነዘቢያ የተነገረበትን የመራጮች መድረክ የመሩት ደግሞ **የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛየ** ሲሆኑ፤ **በዲላ ከተማ** አሥተዳደርም እንዲኹ የመራጭ-ተመራጭ ውይይት ተካሂዷል ተብሏል፤ በዚኽ መድረክ ላይ የተገኙ የአካባቢው ተመራጭ **የተከበሩ ወ/ሮ ዘሪቱ ሽፈራው**፣ ያልተፈቱ እና በሂደት ላይ ያሉ የመልካም አሥተዳደር ችግሮችን በቀጣይ በየደረጃው ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት ደረጃ በደረጃ እንዲፈቱ የበኩላቸውን ድርሻ እንደሚወጡ መናገራቸው ተጠቅሷል።

## የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዜጎች ምን አሉ?

በዚኽ ቅጽ ኹለት ቀዳሚ የእንደራሴ ዕትማችን ሽፋን በሰጠነው ወርኃ የካቲት የእንደራሴዎቹ የውክልና ሥራ ከተካሄደባቸው ክልሎች መካከል ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ይገኝበታል። **በክልሉ ካፋ ዞን ደካ ከተማ**፣ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ የወሩ ብቸኛ የምክክር መካሄዱ ሲሰማ፣ መድረኩን የመሩትም **የተከበሩ ወ/ሮ ተስፋነሽ ወ/ማርያም** መሆናቸው ተጠቅሷል።

**በቢጣ ወረዳ ኦጊዳኪተ ቀበሌ** ከተለያዩ ቀበሌዎች ከተገኙ የኅብረተሰብ ተወካዮች ጋር የመራጭ-ተመራጭ ውይይት ሲካሄድም፣ መንግስት ደረጃ በደረጃ የኅብረተሰቡን ጥያቄ ለመመለስ በትኩረት እየሰራ እንደሚገኝ የምርጫ ክልሉ ተወካይ **የተከበሩ ወ/ሮ ተስፋነሽ ወልደማርያም** ተናግረዋል ተብሏል።




***የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያው የመራጮች መድረክ፤***

## ወደ አፋር ስንሻገር…

በአፋር ክልልም፣ በዚኹ የካቲት ወር የተካሄደው የውክልና ሥራ፣ ልክ እንደ ሱማሌው ክልል ኹሉ አንድ ብቻ ሲሆን፣ ያንንም ያካሄዱት **የተከበሩ ኢ/ር ሀስና ሀንፋሬ** ነበሩ ተብሏል፤ በዚያ **የአይሳኢታ ወረዳ** የመራጭ-ተመራጭ የውይይት መድረክም፣ በሕዝቡ ዘንድ የሚነሱ የመሠረተ-ልማት እና የመልካም አሥተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ በየደረጃው ያሉ አሥፈጻሚ አካላት ትኩረት ሰጥተው መሥራት እንዳለባቸው እንደራሴው ማስገንዘባቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።



*የአፋር ክልሉ የመራጮች መድረክ በከፊል፤*

## 4. የፓርላማው ዲፕሎማሲ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች በወርኃ የካቲት ከከወኑት ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ መካከል ቀዳሚው፣ በቀጣይ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ይካሄዳል የተባለውን **የፓርላማ ኢንተለጀንሲ ሴክዩሪቲ ፎረምን** የተመለከተው ነበር።

የተሳካ የፓርላማ ኢንተለጀንስ ሴክዮሪተ ፎረም ለማካሄድ አስፈላጊው ዝግጅት እንደሚደረግ የተናገሩት ደግሞ፣ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ መሆናቸው ተጠቅሷል። የፓርላማ ኢንተለጀንስ ሴክዩሪተ ፎረም ሊቀመንበር ኮንግረስማን ሮበርት ፒተቴንገርን በጽሕፈት ቤታቸው ያነጋገሩት አፈ-ጉባኤው፣ ፎረሙ ለዓለም ሰላም እና እና ደኅንነት በርካታ አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ ፎረሙ በአዲስ አበባ መካሄዱ ለኢትዮጵያ የፀጥታ እና እና የደኅንነት ተቋማት አስተዋፅኦው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል።

የፓርላማ ኢንተለጀንስ ሴክዮሪተ ፎረም ሊቀመንበሩ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ለዓለም ሰላም እና ደኅንነት ወሳኝ አገር መሆኗን ጠቁመው፣ ፎረሙ ከኢትዮጵያ ጋር በትብብር የሚሰራ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። ፎረሙ በዓለም አቀፍ የበይነ-መረብ ደኅንነት፣ በዓለም አቀፍ ንግድ ደኅንነት፣ በጂኦ-ፖለቲካ ተግዳሮቶች፣ በሕገ-ወጥ የሰዎች እና የማዕድን ዝውውር እንዲኹም በሽብርተኝነት እና ድንበር ዘለል ወንጀሎች ዙሪያ ከዓለም እንደራሴዎች ጋር ውይይት የሚካሄድበት መሆኑን በውይይቱ ወቅት መጠቀሱም ከምክር ቤቱ የወጣው መረጃ ጠቅሷል።



*አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣ ከየፓርላማ ኢንተለጀንስ ሴክዩሪተ ፎረም ሊቀመንበሩ ጋር፤*

የወሩ ኹለተኛ ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ፣ በኢትዮጵያ እና ካናዳ መካከል የእንደራሴዎች ምክር ቤት ወዳጅነት ማኅበርን ለመመስረት የሚያስችል የተባለው ምክክር መካሄዱን የተመለከተው ነበር።

ምክክሩ የተካሄደው በአፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ እና የካናዳ ሴኔት አባል በሆኑት የተከበሩ አሚና ገርባ መካከል መሆኑ ተዘግቧል። በኢትዮጵያ እና በካናዳ መካከል የሚመሰረተው የፓርላማ ወዳጅነት ማኅበር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ያነሱት አፈ-ጉባኤው፣ በኢትዮጵያና በካናዳ መካከል ያለውን ጠንካራ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት በእጅጉ እንደሚያከብሩና፤ በተለይም በካናዳ የሚኖረው የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ በኹለቱ ሕዝቦች መካከል መረዳዳትን በማጠናከር ያደረገው አስተዋፅኦ እጅግ ከፍ ያለ ስለመሆኑም አስረድተዋል ተብሏል።

በካናዳ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ሴኔት አባሉ የተከበሩ አሚና ገርባ በበኩላቸው፣ ካናዳ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዘርፈ ብዙ ግንኙነት ለማሳደግ ፍላጎት እንዳላት መጥቀሳቸው ተዘግቧል።



*አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ እና የተከበሩ አሚና ገርባ*

*እና ልዑካቸው በውይይታቸው ወቅት፤*

## 5. እንደራሴዎቹ ስለ‘ራሳቸው በ‘ራሳቸው

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው የዓመቱ ስድስተኛ ወር፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች የምክር ቤታቸውን የበጀት ዓመቱን የስድስት ወራት የሥራ አፈጻጸም መገምገምን ጨምሮ፣ የተወሰኑ የግንዛቤ ማስበጫ ሥልጠና መድረክም አዘጋጅተው እንደነበር እንደራሴ ከምክር ቤቱ ያሰባሰበችው መረጃ ያመለክታል።

ከዚኽ አንጻርም፣ ቀዳሚው የእንደራሴዎቹ ክንውን የነበረው፣ **የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸም እና የ2017 በጀት ዓመት የተገልጋይ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት** የተገመገመበት ሁነት ነበር።

በዚኽም፣ ባለፉት ሦሥት ዓመታት በተሰሩ የተገልጋዮች የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ ደረጃ መለኪያ የዳሰሳ ጥናቶች መሰረት፣ የተገልጋዩች እርካታ ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል ማሳየቱ ተመላክቷል። በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የዋና ጸሐፊ ተወካይ እና የአሥተዳደራዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊው ከረዩ ባናታ፣ ባለፉት ሦሥት ዓመታት በተሰሩ የተገልጋይ እርካታ ደረጃ መለኪያ የዳሰሳ ጥናቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ የተገልጋዮች የእርካታ ደረጃ መሻሻል ማሳየቱን ገልፀው፣ በቀጣይም ወሰኑን በማስፋት ሊጠና እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል።

በምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት የሙያዊ ድጋፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊው ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻ በበኩላቸው፣ በተቋሙ የተሰጡ ኃላፊነቶችን ለመወጣት የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል ዕቅዶችን በውጤታማነት መፈፀም እንደሚገባ ጠቅሰው፣ በሪፖርት የተመላከቱ ክፍተቶችን ለማረም በልዩ ትኩረት መፈፀም እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል።

የኢፌድሪ የእንደራሴዎች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሥራዎች ዕውን እንዲሆኑ ምክር ቤቱ አስፈላጊውን ክትትል እና ቁጥጥር ያደረጋል ሲሉ የተደመጡበት ደግሞ፣ ሌላደኛው የእንደራሴዎቹ የራስ በ‘ራስ የወሩ ክንውን ነበር። አፈ-ጉባኤው ይህን የገለፁት የምክር ቤቱ የ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ዕቅድ አፈጻጸምን በተመለከተ ከምክር ቤቱ አማካሪ እና አስተባባሪ እንዲሁም የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች በተገኙበት መድረክ ላይ እንደነበረም የምክር ቤቱ መረጃ ያመለክታል። አፈ-ጉባኤው አክለውም፣ የተመረጡትን አጀንዳዎች በውይይት መድረክ በሚበቃ መንገድ ማደራጀትን እና የምክክር መድረኩ የሚመራበትን ስልት ማዘጋጃ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲጠናቀቅ የሚመለከተው የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እያከናወነ ያለውን ድጋፍ እና ክትትል አጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አሳስበዋል ተብሏል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ በበኩላቸው፣ ባለፉት ስድስት ወራት የተሰራው ሥራ በርካታ ለውጦች የተመዘገቡበት ነው ማለታቸው ሲሰማ፤ ምክር ቤቱ በሚያከናውናቸው ሥራዎች እና ኃላፊነቶችን በላቀ ደረጃ በመወጣት የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ሰፊ ሥራ ሰርቷል፤ ለውጥም መጥቷል ብለዋልም ተብሏል።

ሪፖርቱን ያቀረቡት በምክር ቤቱ ፅሕፈት ቤቱ የሙያዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊው ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻም፣ **ሕግ ከማውጣት ጋር በተያያዘ ባለፉት 6 ወራት 16 ዐዋጆች ለምክር ቤቱ ቀርበው፣ ከነዚህ ውስጥም 12 ዐዋጆች መጽደቃቸውን** በሪፖርታቸው ጠቅሰዋል። ቀሪዎቹ 4

ዐዋጆች ደግሞ በምክር ቤቱ የሕግ አወጣጥ ሂደት ላይ መሆናቸውን መጥቀሳቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የፌዴራል ሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ **“የሕግ አውጭው አካል አርዓያነት፣ ለፀረ-ሙስና ትግል ያለው ፋይዳ”** በሚል ርዕሰ-ጉዳይ ዙሪያ፣ እንደራሴዎቹ የታደሙበት አንድ የአቅም ግንባታ ሥልጠና መድረክም በወሩ ከተካሄዱ እንደራሴዎቹ ተኮር ክንውኖች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው ነው።

በዚኹ የሥልጠና መድረክ ላይ የተገኙት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ በኢትዮጵያ ተቋማዊ እና መንግስታዊ ሙስና አለመኖሩን አንስተው፣ ከአገልግሎት አሰጣጡ ጋር በተያያዘ እየተከሰቱ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ደግሞ ሙስናን የሚጠየፍ ትውልድ ለመፍጠር በየደረጃው ያሉ አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል ተብሏል።

የአገር እና የሕዝብን አደራ ለመወጣት የተቋማት ኃላፊዎች በታማኝነት ሕዝባቸውን እያገለገሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ምክር ቤቶች ሚናቸውን በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸውም ምክትል አፈ ጉባኤዋ አስገንዝበዋል፡፡ ኢትዮጵያ የያዘችው የብልፅግና የዕድገት ጉዞ እውን እንዲሆን ሁሉም ዜጋ ለፀረ-ሙስና ትግሉ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበት በመድረኩ ላይ ተናግረዋል የተባሉት ደግሞ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ እውነቱ አለነ ነበሩ።

## 6. እንደራሴዎቹ እና ምርጫ 2018

የኢትዮጵያ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በዚኹ የካቲት ወርም ቀጣዩን ምርጫ 2018 አስመልክቶ የተለያዩ ክንዋኔዎችን መከወኑን ምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። ከእነዚኽም መካከል ሊጠቀስ የሚችለው አንደኛው ክንውን፣ በምክር ቤት **የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፤** ቀጣዩ ምርጫ ዲሞክራሲያዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ ስላለባቸው አገራዊ **ኀላፊነት ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን አመራሮች ጋር ውይይት** ማድረጋቸው ነበር።

በዚኹ የውይይት መድረክ ላይ የተገኙት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ 7ኛው አገራዊ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ እንዲጠናቀቅ መገናኛ ብዙኃን ሕግ በማክበር፣ ሙያዊ የሥነ-ምግባር መርሆዎችን እና ሞያዊ ግዴታዎችን አንግበው መሥራት እንዳለባቸው ተግረዋል ተብሏል። በተጨማሪም ምርጫው ተዓማኒ፣ ፍትሓዊ፣ ግልጽ እና ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ከቅድመ-ምርጫ አንስቶ ያሉ ሂደቶችን ኹሉንም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ መዘገብ የመገናኛ ብዙኃን ዋነኛ ተግባር መሆን እንደሚገባው አስረድተዋል። በመድረኩም የተቋሙ የማሻሻያ ተግባራት እና ቀጣይ ስትራቴጂካዊ የትኩረት መስኮች በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተሯ ወ/ሮ ሀይማኖት ዘለቀ ቀርቦ በምክር ቤቱ አባላቱ ሐሳብ እና አስተያየት ተሰጥቶበታል።



***የውይይት መድረኩ በከፊል፤***

ሌላይኛው ምርጫ ተኮር ተያያዥ ኹነት፣ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ የተናገሩበት አንድ መድረክ መሆኑ ተጠቅሷል። "የዳኝነት እና ዴሞክራሲ ተቋማት አመርታ፤ ለተሳካ አገረ መንግሥት ግንባታ!" በሚል መሪ ሐሳብ በዳኝነት እና ዴሞክራሲ ተቋማት ቅንጅት ላይ ባተኮረው አገራዊ መድረክ ላይ የተገኙት አፈ-ጉባኤው፣ 7ኛው አገራዊ ምርጫ ነፃ፣ዴሞክራሲያዊ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በርካታ አስቻይ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል ማለታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው ዘገባ ጠቅሷቸዋል።



**አፈ-ጉባኤው የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ በውይይቱ ወቅት፤**

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ላይ የተከናወኑ መሠረታዊ የለውጥ እርምጃዎች የአገሪቱን የዴሞክራሲ ሥርዓት ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋገሩ ናቸው ያሉት የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ምክር ቤቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅን በማሻሻል፣ ቦርዱ ያለምንም ጣልቃ ገብነት በነፃነት እንዲሠራ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን ገልጸዋል ተብሏል።

# 7. የብሪጅ ዳሰሳዊ ምልከታ፦ በአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ እና ተያያዥ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ

ኢትዮጵያውያን በብዙ ተስፋም፣ በከፊል ጥርጣሬም እየተመለከቱት ያለው የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን፣ በተለያዩ ድርብርብ ምክንያቶች የተነሳ ባቀደው ልክ መጓዝ አለመቻሉ በወርኃ የካቲት አጋማሽ ላይ ተሰምቷል። ይኽን ግንዛቤ ውስጥ የከተተው የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤትም፣ የኮሚሽኑን ተግዳሮቶች አሳማኝ ሆነው ስላገኛቸውም የተቋሙን ዕድሜ በስምንት ወራት አራዝሟል። ምክር ቤቱ ለ8 ወራት እንዲራዘም የቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ በሙሉ ድምፅ አጸድቆታል። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የካቲት 11 2018 ዓ.ም. ባካሄደው የ5ኛ ዓመት የስራ ዘመን 1ኛ አስቸኳይ ስብሰባው፣ ኮሚሽኑ የእስካሁን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ በመወያየት ቀጣይ አቅጣጫዎችንም አስቀምጧል። ይኽች የእንደራሴ ኹለተኛ ዓመት የመጀመሪያ ዕትምም፣ ይኽን የእንደራሴዎቹን ውሳኔ ተንተርሳ፣ በአገራዊ ምክክር ምንነት፣ በኮሚሽኑ ተግዳሮቶች እና የተቋማችን ምክረ-ሐሳቦች አጠቃልላ በሚከተለው መልኩ ሰፋ ያለ ትንታኔ መስጠትን መርጣለች።

## ለምን ወደ ምክክር?

በአገራዊ ምክክር አስፈላጊነት ዙሪያ የተጻፉ ብዙ ድርሳናት እንደሚያወሱት፣ አገራት ብሔራዊ ምክክርን እንዲያካሂዱ የሚያስገድዷቸውን ሁኔታዎች ሲዘረዝሩ በዋናነት የሚጠቅሱት፣ የአንድ አገር መሠረት ወይም የመንግሥት ሕጋዊ ቅቡልና አደጋ ላይ ሲወድቅ መሆኑን አበክረው ያነሳሉ። ያን መሰል አደገኛ ኹኔታ ሲገጥምም፣ አገራዊ ምክክሩ በመንግሥት፣ በፖለቲካ ተዋናዮች እና በኅብረተሰቡ መካከል ያለውን ማኅበራዊ ውል እንደገና መቅረጽን ዓይነተኛ ግቡ አድርጎ ይካሄዳል። ከዛ ባለፈም፣ በለውጥ እና በነባር ኃይሎች መካከል የበረታ ፍጥጫ ሲገጥምም ልሂቃኑ ወደ ምክክር ለመሄድ ተጨባጭ ግፊት እንደሚገጥማቸው ይነሳል። ከዚሑ ጋር በተያያዘም፣ እንደ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች፣ አድማዎች ወይም አብዮቶችን መሰል ከታች ወደላይ የሚነሱ ሰፊ መሠረት የያዙ ግፊቶች መንግሥታትን ወደ ምክክር ጠረጴዛ እንዲመጡም ያስገድዳሉ። ሌላው ሳይጠቀስ የማይታለፈው፣ በትጥቅ ግጭት ወይም በከፍተኛ ፖለቲካዊ አለመግባባት ወቅት ውጥረትን ለማርገብ እና ወደ ሰላማዊ ሽግግር ለመግባት አገራት ፊታቸውን ወደ ምክክር ያዞራሉ።

ምንም እንኳን ብሔራዊ ምክክር እንደ ሳይንሳዊ የጥናት ዘርፍ በቅርብ ጊዜ ጎልቶ ቢወጣም፣ በተግባር ግን ለበርካታ ዐሥርታት በተለያዩ አገራት ሲሠራበት ቆይቷል። በተለይም በደቡብ አፍሪካ፣ ከአፓርታይድ በኋላ የተደረገው የሽግግር ፍትሕ ሂደት እና የዕውነት እና የእርቅ ኮሚሽን ምስረታ ለዓለም የቅርብ ዘመኑ ትልቅ ተሞክሮ ሆኗል። ከደቡብ አፍሪካ ባለፈም፣ እንደ ቤኒን፣ ጋቦን፣ ኮንጎ፣ ቶጎ፣ ማሊ እና ኒጀር ያሉ አገራት የኢኮኖሚ ቀውስን እና የፖለቲካ ተቀባይነት ማጣትን ለመፍታት በተለያዩ ዘመናት ብሔራዊ ጉባኤዎችን አካሂደዋል። ከዓረቡ አብዮት በኋላ በቱኒዚያ እና የመን የተደረጉት ምክክሮችም የፖለቲካ ሽግግርን ለመምራት በጉዳዩ ላይ የተጻፉት ድርሳናት እንደ ተጨማሪ ምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

የአሜሪካ የሕገ-መንግሥት ቀረጻ ሂደት፣ የፖርቱጋል እና የስፔን የ1970ዎቹ የሽግግር ሂደቶች፣ እንዲሁም በታይላንድ፣ አፍጋኒስታን እና ኔፓል የተከናወኑ ተግባራት የብሔራዊ ምክክር መልክ ያላቸው ሂደቶች እንደነበሩም ይታወሳል። ከቶጎ እስከ የመን ባሉት ሂደቶች እንደታየው፣ አገራዊ ቀውሶችን ለመፍታት እና አካታች የሆኑ ድርድሮችን ለማካሄድ፣ አገራዊ እጅግ ተመራጭ መንገድ እየሆነ መጥቷል። ሂደቱ የተሳካ የሚሆነው ግን ኹሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ማካተት ሲችል እና ግልጽ የሆነ የፖለቲካ ስምምነት ላይ መድረስ ሲችል መሆኑን ልብ ይሏል።

## ኢትዮጵያን ወደ ብሔራዊ ምክክር የመራት ምንድር ነው?

ኢትዮጵያን ወደ ብሔራዊ ምክክር የመራት ለዘመናት የተከማቹ ውስብስብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ቅራኔዎች

መሆናቸው አሌ አይባልም። ጠቅለል አድርገን እንመልከታቸው ስንልም፣ ከታሪክ ቁስሎች እስከ የማንነት ጥያቄዎች ድረስ ረዘም ያሉ ያልተፈቱ ስር ያላቸው ውዝግቦች መሆናቸውን እንመለከታለን። ኢትዮጵያ በታሪኳ ለችግሮቿ ዘላቂ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ ኃይልን እንደ መሣሪያ ስትጠቀም ቆይታለች። ሥልጣን የሚያዘው እና የሚጠበቀው በጉልበት በመሆኑ፣ የአሸናፊዎች ፍትሕ ባህል ሰፍኖ ቆይቷል። በተለይም በዳግማዊ አፄ ምኒልክ የማስፋፋት ሂደት፣ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ማዕከላዊ አስተዳደር እና በደርግ ጭቆና ወቅት የተፈጠሩ ቅሬታዎች እስካሁንም አልተፈቱም።

ከ1983 ወዲህ የሰፈነው በብሔር ላይ የተመሰረተ ፌዴራሊዝም፣ የታሪክ በደሎችን ለመመለስ ያለመ ቢሆንም፣ አዳዲስ የብሔር ግጭቶችን፣ የሥልጣን ሽኩቻን እና የሀብት ክፍፍል ቅራኔዎችን ወልዷል። ይህ ሦሥት ዐሥርት ያለፈው ሥርዓትም አገራዊ አንድነትን ከመፍጠር ይልቅ ልዩነትን አጉልቷል ተብሎ በአንዳንዶች ይተቻል። ከስምንት ዓመታት በፊትም፣ በተለይም በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች የተቀሰቀሱት ሰፊ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች የቀድሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝን ለሥልጣን መልቀቅ እና የዶ.ር ዐቢይ አሕመድን አሥተዳደር ወደ ሥልጣን እንዲመጣ ምክንያት ሆነዋል። በፌዴራል መንግሥቱ እና በሕወሓት መካከል የተደረገው አስከፊው የሰሜኑ ጦርነትም ከፍተኛ ሰብዓዊ ቀውስ አስከትሏል። ከእነዚህ በተጨማሪም፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች የተስተዋሉት የትጥቅ ግጭቶች፣ እንዲሁም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በሶማሌ፣ በደቡብ እና በአፋር ክልሎች የሚታዩ የማንነት እና የሀብት ግጭቶች አገሪቱን ወደ ምክክር እንድትገባ አስገድደዋታል ቢባል ተጨባጩን ሃቅ አጠር አድርጎ ማቅረብ ብቻ ይመስለናል።

## ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ፦ የጎርዲያኑ ቋጠሮ?

ብዙዎች ብዙ እያሉበት ያለው እና ቀጣዮቹ ስምንት ወራት ወሳኝ ናቸው የተባለለት አገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ፣ እስከዛሬ ከሰበሰባቸው አጀንዳዎች አኳያ እና ከነባሩ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አኳያ፣ ከባዱ ተግዳሮቱ በሕገ-መንግሥቱ ዙሪያ ሊያካሂድ የሚችለው አገራዊ ምክክር እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። የተሰበሰቡት አጀንዳዎችም ሆኑ፣ በቀጣይ የአጀንዳ ማሰባሰብ ይካሄድባቸዋል ተብለው ከሚጠበቁት ክልሎች እና አካባቢዎች አንጻርም ስንመለከትም፣ እጅግ ብዙዎቹ አጅንዳዎች እና ቀጣይ ተሳታፊዎች ምክክር ያስፈልጋቸዋል ብለው የሚያነሷቸው አጀንዳዎች በአንድ ሰነድ ዙሪያ የሚሽከረከሩ ይመስላል፤ በሕገ-መንግሥቱ ዙሪያ። ይኽን ርዕሰ-ጉዳይም፣ የምክክር ኮሚሽኑ የጎርዲያን ቋጠሮ* ብለን ብንሰይመው ከእውነቱ ብዙም አንርቅም።

ባለፉት ብዙ ዓሥርታት የተካሄዱት የፖለቲካ ግጭቶች በኢትዮጵያ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሰዋል። ይህም በእጅጉ የተከፋፈለችውን አገር ወደ አንድ ለማምጣት የሚደረጉ ረዥም ጥረቶችን አስከትሏል። በኢትዮጵያ የተለያዩ ሕዝቦች መካከል በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ስምምነት አለመኖሩም ለአገረ-መንግሥቱ አለመረጋጋት መሠረታዊ ምክንያት ሆኗል። በተለይም የ1987ቱ የፌዴራል ሕገ-መንግሥት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ፣ ሰነዱ አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል። በብሔር እና በቋንቋ ላይ የተመሰረተው የመንግሥት መዋቅር እንዲሁም ለ“ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች” የተሰጠው የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ስፋት ዋነኛው የአለመግባባት ማዕከሎች ናቸው። የሥርዓቱ ደጋፊዎች እና ተቺዎች መካከል ያለው ልዩነት በ2010 ከተካሄደው የፖለቲካ ሽግግር በኋላም ይበልጥ ጎልቶ ታይቷል። የብልጽግና ፓርቲም፣ ሕገ-መንግሥታዊ ቀውሱን የመፍታትን አስፈላጊነት እንደሚገነዘብ እና በስምምነት ላይ የተመሰረተ የሕገ-መንግሥት ማሻሻያን እንደሚደግፍም ሲገልጽ ተስተውሏል።

መንግሥት አስፈላጊውን ስምምነት ለመፍጠር የመረጠው መንገድ ብሔራዊ ምክክርን ሲሆን፣ ይህም ከሦሥት ዓመታት በፊት በእንደራሴዎች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ሲቋቋም የተጀመረ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሕገ-መንግሥቱን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ወደ ምክክሩ እየተመሩ

ሲሆን፣ ማሻሻያ እንዲደረግ የሚቀርቡ ጥሪዎችም እውን የመሆን ዕድል ያላቸው ይመስላሉ። በመሆኑም ብሔራዊ ምክክሩ ለሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ ወሳኝ ምክንያት ሊሆን ይችላል ተብሎም ተገምቷል። በመጀመሪያ ደረጃ የማሻሻያ አስፈላጊነት መኖሩን እንደሚያረጋግጥ እና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የሚፈለጉትን የለውጥ ዝርዝሮች እንደሚያሰባስብ ይጠበቃል። በተጨማሪም ምክክሩ በተለያዩ አመለካከቶች ባሏቸው ተሳታፊዎች መካከል ስምምነትን ለመፍጠር ያለመ ነው። አገሪቱ ያለችበትን ጽንፍ የረገጠ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ይህንን ግብ ማሳካት ያለውን አስቸጋሪነት አሳንሶ ማየት እንደማይቻል ግን ማስታወስ ያሻል።

**_*የጎርዲያን ቋጠሮ (Gordian Knot) የሚለው አገላለጽ መነሻው ጥንታዊው የግሪክ ተረታ-ተረት ሲሆን፣ ትርጉሙም እጅግ ውስብስብ እና በቀላሉ የማይፈታ ችግርን ያመለክታል። ተረኩ እንደሚለው፣ የፍርግያ ንጉሥ የነበረው ጎርዲየስ ጋሪውን ከእንጨት ምሶሶ ጋር በጣም ውስብስብ በሆነ ቋጠሮ ያስረዋል፤ ቋጠሮውም የገመዱ ጫፎች የማይታዩበትና ማንም ሊፈታው የማይችል ነበርም ተብሏል። ቋጠሮውን እንዲያ ካጠበቀው በኋላም፣ “ይህንን ቋጠሮ የፈታ የእስያ ንጉሥ ይሆናል” የሚል ትንቢትም መናገሩ ተጽፏል። ይኽን ትንቢት እየሰማ ያደገው ታላቁ እስክንድርም፣ በተለመደ ኹሉን ቻይ ጥማቱ ቋጠሮውን ሊፈታው ሻተ። በ333 ዓ.ዓ. ላይ ወደ ፍርግያ የመጣው እስክንድር፣ ቋጠሮውን ለመፍታት ብዙ ቢሞክርም አልተሳካለትም። በመጨረሻም እስክንድር የተለየ መፍትሔ አመጣ፤ ተረታ ተረቱ እንደሚለውም፣ ሰይፉን መዝዞ ቋጠሮውን በመቁረጥ ለሁለት ሲሰነጥቀው ገመዱ ወዲያው ተፈታ። የዚኽ ተረክ ትዕምርታዊ ትርጉምም፣ አንድን ውስብስብ ችግር በቀጥታ እና ባልተለመደ ደፋር እርምጃ መፍታትን ያመለክታል።_**

ሰፊ መሠረት ያለው ብሔራዊ ምክክር አስፈላጊነት በሰፊው ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ አካታች የሕዝብ ተሳትፎ ለስኬታማ የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ሂደት ቁልፍ ነው። ሆኖም አሁን ያለው ምክክር እውነተኛ ስምምነት ሊያመጣ ወይም ለሕገ-መንግሥታዊ ቀውሱ መፍትሔ ሊሰጥ ይችላል ብለው የሚጠራጠሩ ብዙዎች ናቸው። እንዲያውም በቂ ስምምነት ሳይኖር የሚደረግ ማሻሻያ ግጭቱን ሊያባብሰው ይችላል የሚሉ ስጋቶች ከተለያዩ ፖለቲከኞች እየቀረቡ ነው።

ምክክሩ በብሔራዊ ጉዳዮች ላይ ልዩነት ያላቸውን የፖለቲካ እና የአስተያየት መሪዎችን እንዲሁም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ወደ ሕዝባዊ ውይይት በማምጣት ብሔራዊ ስምምነትን ለመፍጠር ያልማል። አሥራ አንድ አባላት ያሉት ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን የእነዚህን ልዩነቶች መንስኤ የመለየት፣ አጀንዳዎችን የመቅረጽ እና በክልል እና በብሔራዊ ደረጃ አካታች መድረኮችን የማመቻቸት ሥልጣን ተሰጥቶታል። ኮሚሽኑ በምክክሩ ውጤቶች ላይ በመመስረት የውሳኔ ሐሳቦችን የማቅረብ፣ እንዲሁም አፈጻጸማቸውን የመደገፍ እና የመከታተል ኃላፊነትም አለበት። ከተሰጠው ሰፊ ተግባር በተጨማሪ ኮሚሽኑ በትከሻው ላይ ብዙ ሸክሞችን ተሸክሟል። ይህም የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ የወደፊቱን የኢትዮጵያ መንግሥት መዋቅር የሚወስን በመሆኑ አገሪቱን ወደ ሰላም ወይም ወደ ተጨማሪ ጦርነት ሊመራት የሚችል ትልቅ ፋይዳ ስላለው ነው። የኮሚሽኑ ግኝቶች እና ጥቆማዎች ለሕገ-መንግሥታዊ ለውጦች እና ለሚከተሉት ሂደቶች መሠረት የመሆን ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ማንኛውም የሚመጣ ማሻሻያ ተቀባይነት እንዲኖረው በኮሚሽኑ ላይ ያለው የሕዝብ አመኔታ እንደ ገለልተኛ አስታራቂነቱ ወሳኝ መሆኑን አንስተን እንለፍ።

ከዚህ አንጻር በርካታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኮሚሽኑ ከመንግሥት ያለውን ነፃነት ሲተቹ እና የሂደቱን ቅንነት ሲጠራጠሩ ቆይተዋል። የሚያሳስበው ደግሞ በርካታ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በምክክሩ ላይ ላለመሳተፍ መወሰናቸው እና መውጣታቸው ነው። ምንም እንኳን ብዙ ፓርቲዎች በኋላ ላይ ቢመለሱም፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች አጀንዳ በሚሰበሰብበት ወቅት ተሳትፎው እንደገና እየቀነሰ መጥቷል። በታኅሣሥ ወር የእናት ፓርቲ፣ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)ን ጨምሮ ሰባት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሁለት የተለያዩ መግለጫዎች የብሔራዊ ምክክሩ ስኬታማ የመሆን ዕድል እየጠበበ መምጣቱን ገልጸዋል። ያም ሆኖ በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ ተሳታፊ ያልሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወደ ምክክሩ ለመመለስ ጥረት እያደረገ ነው። ከጥቂት ወራት በፊትም ኮሚሽኑ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ፣ ከሦስት የፖለቲካ ፓርቲዎች

ማለትም ከኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)፣ ከመኢአድ እና ከእናት ፓርቲ ጋር ውይይት ማድረጉን ገልጾ፣ ሁሉም ፓርቲዎች ግን ለመመለስ ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጠዋል። እነዚህም ቀጣይነት ያላቸው ግጭቶች በሰላም እንዲፈቱ እና ተዋጊዎች በብሔራዊ ምክክሩ እንዲካተቱ፣ እንዲሁም የተገለሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የታሰሩ ፖለቲከኞች፣ ጋዜጠኞች እና አክቲቪስቶች በምክክሩ እንዲሳተፉ የሚሉ ናቸው። ፓርቲዎቹ እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት በዋነኛነት በመንግሥት አካላት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ያምናሉ። ኮሚሽኑ በአሁኑ ወቅት ከተሳትፎ ውጪ ያሉ ሌሎች ፓርቲዎች ጋር ውይይቱን እንደሚቀጥልም ገልጿል።

በዚኽ ንዑስ ርዕስ ስር ከጠቀስነው የሕገ-መንግሥቱ የጎርዲያን ቋጠሮነ አንጻርም፣ የተለያዩ አመለካከቶች በአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ላይ ታይተዋል። ለምሳሌ በኦሮሚያ ተሳታፊዎች ካነሷቸው ነጥቦች መካከል የመዲናዋ አዲስ አበባ ወደ ኦሮሚያ መጠቃለል፣ የመገንጠልን መብት ጨምሮ የብሔሮች ራስን የመወሰን መብቶች መጠበቅ እና አከራካሪው ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ የብሔር እኩልነት ምልክት በመሆኑ ሳይለወጥ እንዲቆይ የሚሉ ይገኙበታል። እነዚህ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌዎች በአማራው ክልል መድረኮች ላይ ደግሞ የበረታ ተቃውሞ ገጥሟቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ መሰል ልዩነቶቹ በፌደራሎቹ ክልሎች መካከልም ተስተውለዋል። በክልል ደረጃ የብሔር ራስን የመወሰን ድጋፍ በኦሮሚያ፣ በሶማሌ እና በደቡብ በሚገኙ አዳዲስ ክልሎች ዘንድ ድጋፍ ሲኖረው፤ በአማራ ክልል ደግሞ ሕገ-መንግሥቱ ከልክ በላይ በብሔር ላይ ያተኮረ ነው በማለት ማሻሻያ እንዲደረግ መጠየቅ ተጀምሯል። ሂደቱ ከቀጠለ አሥራ ሁለቱም ክልሎች በሆነ መንገድ በማሻሻያው ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ይኖራቸዋል። በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተቀመጡት የማሻሻያ ድንጋጌዎች በጥብቅ የሚከተሉ ከሆነ፣ ማንኛውም ክልል የፌዴሬሽኑ እኩል አባል እንደመሆኑ መጠን በብሔር ራስን ማስተዳደር መብቶች ላይ የሚቀርቡ የማሻሻያ ሐሳቦችን ውድቅ የማድረግ ሕገ-መንግሥታዊ አቅም አለው። በዚህ ረገድ ስምምነት ላይ መድረስ እያንዳንዱ ክልል ለብሔራዊ አንድነት ሲባል የራስን ማስተዳደር መብቱን በተወሰነ ደረጃ መተው ሳይጠበቅበት አይቀርም፤ ይህ ደግሞ ቢያንስ በአሁኑ ተጨባጭ ኹኔታ ሊሆን የማይችል ይመስላል።

በቅርብ ጊዜ ውስጥ በሆነ መንገድ ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያ ሊደረግ የሚችልበት እውነተኛ ተስፋ ቢኖርም፣ ግጭቶችን በማለዘብ እና ሰላምን በማምጣት ረገድ ያለው የስኬት ዕድል ግን ሩቅ ይመስላል። እንዲያውም የሕገ-መንግሥት ለውጥን የሚደግፉትን ጨምሮ ብዙዎች አሁን ያለው የማሻሻያ መንገድ ትርምሱን ሊያባብሰው ይችላል የሚል ስጋት አላቸው፤ ከብሔር ፌዴራሊዝም በድንገት የመውጣት አደጋዎችም ከበርካታ ወገኖች በተደጋጋሚ ሲነሱ ይደመጣሉና።

## ምን ተብሎ ነበር?

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ፣ ባሳለፍነው የካቲት ወር ዕድሜዬ ይራዘምልኝ ሲል ያቀረባቸውን ዋና ዋና ምክንያቶች ከማየታችን በፊት፣ ከዚኽ ቀደም በኮሚሽኑ ከተነገሩት ውስጥ ከዓመት በፊት የተነገረውን ብንጠቅስ ርዕሰ-ጉዳያችንን ምልዑ ያደርግልናል። ኅዳር 10 2017 ዓ.ም. ላይ የተሰበሰበው የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በዚኹ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ እንደነበር ይታወሳል። በወቅቱም፣ ኮሚሽኑ በትግራይ ክልል አጀንዳ እና ተሳታፊዎችን ለመለየት የእንደራሴዎቹ ምክር ቤትን እገዛ እንደሚፈልግ ገለጾ ነበር። የምክር ቤት አፈ ጉባኤ ታገሰ ጫፎ በበኩላቸው "አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር ጠንካራ ሥራ በጋራ ተቀናጅተን እንሠራለን። ከክልሉም ጋር እንመካከራለን" ብለዋል። የኮሚሽኑ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያም፣ ኮሚሽኑ ያከናወናቸውን እና ቀሪ ሥራዎች ለምክር ቤት አባላት አብራርተው ነበር። "ዛሬ ላይ ለአናንተ ሥራችንን ጨርሰን የምንወጣበትን ሪፖርት ነበር ማቅረብ ያለብን" ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ፣ ተቋማቸው ይህን እንዳያደርግ ምክንያት የሆኑ ክፍተቶችንም ጠቃቅሰው ነበር። ባለፉት ሦስት ዓመታት በተለያዩ ቦታዎች ያጋጠሙት ሁኔታዎች ከእነዚህ ክፍተቶች መካከል መሆናቸውን ፕ/ር መስፍን ገልጸዋል። "ምዕራብ ኢትዮጵያ ችግር በነበረበት ወቅት ነው የእኛ ሥራ የተጀመረው" ያሉት ዋና

ኮሚሽነሩ፤ “ምዕራብ ኦሮሚያ በተመሳሳይ መልኩ ችግሮች ያጋጥማሉ። አማራ ስንጀምር ችግር አልነበረም፤ በአሁኑ ሰዓት ግን አስቻይ ሁኔታ እና አንጻራዊ የሆነ ሰላም ያስፈልጋል” ብለዋል። ፕሮፈሰር መስፍን ምዕራብ ኢትዮጵያ ነበር ያሉት ችግር ተቀርፎ ኮሚሽኑ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ሥራውን ሙሉ በሙሉ ማጠናቀቁን ጠቅሰው፣ በትግራይ ክልል ያለውን ሁኔታም በዚያ ሪፖርታቸው ጠቅሰውት ነበር።

ዋና ኮሚሽነሩ “የትግራይ አረጋዴ መብራት አግኝተን ሙሉ በሙሉ ሥራዎች መሠራት አለባቸው፤ ግን በዚያ በኩል ደግሞ የሚቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ፤ ይህ እንግዲህ የሕዝብ ተወካዮች ኃላፊነት ነው ብለን ነው የምናምነው” ብለዋል። “ከትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዝዳንት ጋር የተወሰነ ጊዜ በመውሰድ መክረናል” ያሉት ፕ/ር መስፍን፤ “በዚያ ምክክር ላይ የተግባባነው ነገር ቢኖር ይህን የአገራዊ ምክክር ሂደት በእርግጥም እንደሚያምኑበት፣ የአገራዊ ምክክር ሂደትን በመርኅ ደረጃ እንደሚቀበሉት እና ተገቢ እንደሆነም ነግረውናል” ሲሉ ተናግረዋል። ዋና ኮሚሽነሩ አክለውም “ሁኔታዎች በሚመቻቹበት ጊዜ ካቢኔውን እና የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን እንደምናነጋግር እና እንደሚያገናኙን ቃል ገብተውልን ነበር” ብለዋል። ከፕሬዝዳንቱ ጋር ተደጋጋሚ ስብሰባዎች መደረጋቸውን የጠቀሱት ፕ/ር መስፍን ለምክር ቤት አባላቱ “ግልጽ በሆነ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ወደ ትግራይ የገባንበት አካሄድ የለም” ብለዋል። ዋና ኮሚሽነሩ ለተወካዮች ምክር ቤት አባላት “ግልጽ ናቸው” ያሏቸውን ምክንያቶች ግን አልዘረዘሩም።ኮሚሽኑ ከትግራይ ክልል ነዋሪዎች ጋር ውይይቶችን ባያደርግም ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና በክልሉ ከሚገኙ የዩኒቨርሲቲ አመራሮች ጋር ውይይቶች መደረጋቸውን ዋና ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል።

ፕ/ር መስፍን ሪፖርታቸውን ካቀረቡ በኋላም እንደራሴዎቹ ጥያቄዎችን አቅርበዋል። የቀረቡት ጥያቄዎች በዋናነት ከታጠቁ ቡድኖች ተሳትፎ፣ የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን እንዲሁም የአማራ፣ የኦሮሚያ እና የትግራይ ክልል ተሳታፊዎች እና አጀንዳ ልየታ ላይ ያተኮሩ ነበሩ። በዚያ ዕለትም ፕ/ር መስፍን በቀሩት ሦስት ወራት ውስጥ አወያይታችሁ፣ ምክረ ሃሳብ ሰብስባችሁ ሪፖርት በማቅረብ ታጠናቅቃላችሁ ወይ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ “እኛ የካቲት 14/2014 ቃለ መሃላ ስንፈጽም ከአንድ ሰዓት በኋላ አፈ ጉባኤው በመሩት ስብሰባ ላይ ተገኝተን ስንነጋገር ቃል የገባነው በሦስት ዓመት ውስጥ ሥራችንን ልንጨርስ ነው። ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ሥራችንን እየሠራን አገባደን እናንተ ፊት መቅረብ ነው የእኛ አጀንዳ” ሲሉ መልሰውም ነበር። ዋና ኮሚሽነሩ አክለውም “ጊዜን በተመለከተ እኛ ይሄን ያህል ጊዜ ይሰጠን ወይም እንዲህ ይደረግልን ለሚለው ጥያቄ አይደለም ዝግጁነታችን። እኛ ዝግጁነታችን አሁንም በዚህ በቀረን ጊዜ ሠርተን የት መድረስ እንችላለን የሚል ነው” ብለዋል። የኮሚሽኑን የሥራ ጊዜ ማራዘምን በተመለከተም፤ “ስታቋቁሙ እናንተ ናችሁ ያቋቋማችሁት፤ ሦስት ዓመት ብላችሁ የወሰናችሁት እናንተ ናችሁ። ከዚህ በኋላ ይብቃኝ ማለት መብት አላችሁ፤ ይቀጥል ማለትም መብት አላችሁ። ስለዚያ ምንም እኛ የምንለው ነገር የለም። ነገር ግን በጊዜ ሂደት ከአፈ ጉባኤው እና ከሚመለከታችሁ አመራሮች ጋር ቁጭ ብለን በዝርዝር የምናስረዳበት ሂደት ግን አለ” ሲሉ አብራርተዋል።

## ለምን ይራዘምልንስ አሉ?

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ለአንድ ዓመት የተራዘመለት የሥራ ጊዜው ሊያበቃ አንድ ሳምንት ብቻ ሲቀረው፣ ለቀጣዮቹ ስምንት ወራት ይራዘምለት ዘንድ እንደራሴዎቹ ፍቃዳቸው ሆኗል። ኮሚሽኑ ሥራውን እንዲያጠናቅቅ በሚል የኢትዮጵያ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባለፈው ዓመት የካቲት 11፤ 2017 ዓ.ም ባደረገው አስቸኳይ ስብሰብ ነበር ጊዜው ለአንድ ዓመት ያራዘመው። ኮሚሽኑ የግማሽ ዓመት ሥራውን በምክር ቤቱ ለዴሞክራሲ ፓዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲያቀርብ እስካሁን የተሰበሰቡ አጀንዳዎች በሚገባ ተብላልተው በተረጋጋ ኹኔታ መታየት ያለባቸው በመሆኑ ጊዜ እንደሚያስፈልገው ገልጿል። እስካሁን የኮሚሽኑ ሥራ ያልተጀመረበትን ትግራይ ክልል በተመለከተም የግድ

መሳተፍ እንዳለበት ተገልጾ፣ ሕዝብ መታገት የለበትም በሚልም ማብራሪያ ተሰጥቷል።

ኮሚሽኑ የስድስት ወራት ሥራውን አርብ ጥር 29 ቀን 2018 ዓ.ም. በኢንደራሴዎቹ ምክር ቤት ለሚገኘው የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሲያቀርብ ይህ ርዕሰ ጉዳይ ጉዳይ ዋነኛ መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። ተቋሙ አጀንዳ የመሰብሰብ ሥራው ተጠናቆ ጥር 2018 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ዋናው ምክክር ለመግባት አቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ ሥራው በትግራይ ክልል ባለመጀመሩ የምክክሩ ጉባኤው መቼ እንደሚጀመር ለመግለጽ አስቸጋሪ እንደሆነበት ጠቅሷል። ኮሚሽነር ዘገየ አስፋውም፣ ይህንን በስፋት ካነሱት የተቋሙ መሪዎች አንዱ ነበሩ። እርሳቸውም፣ "በመቻኮል ፍሬ ቢስ እንዳናደርገው አታቻኩሉን" ብለዋል። ይህንን በታላቅ ተስፋ ሕዝብ የሚጠባበቀውን ያሉትን የምክክር ሥራ ውጤት ጊዜ አሳጥረን ውሽልሽል ነገር ማቅረብ የለብንም ያሉት ኮሚሽነር ዘገዬ፣ የተሰበሰበውን አጀንዳ ለመለየት ራሱ ከፍተኛ ችግር እንደሆነ እና አጀንዳ ለመለየት ሥነ ሥርዓት ብናበጅም ገና አልገባንበትም የሚለው ለዚህ አቋማቸው ተጨማሪ ምክንያት እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ሌላኛው ኮሚሽነር አምባሳደር መሐሙድ ድሪር በፊናቸው፣ ሥራው በትግራይ ክልል አለመጀመሩን መነሻ በማድረግ ሕዝብ መታገት የለበትም ሲሉ አሳስበዋል። በትግራይ ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ እና ተከትሎ ያሉትን ሥራዎች ከክልሉ ውጪም ቢሆን ኮሚሽኑ ለምን በሚመቸ ቦታ አያደርግም በሚል ለቀረበለት ጥያቄ ይህ የሚሆን እንዳልሆነ ዋና ኮሚሽነሩ ምላሽ ሰጥተዋል። “ምክክር መቼ ያልቃል? በቀላሉ የሚገመት እና የሚነገር ሂደት አይደለም"ም ብለዋል። አክለውም በሚቀጥሉት ወራት እንዴት ማስጀመር እንችላለን ሲሉ የምክር ቤቱን ከፍተኛ እገዛ እንሻለን ሲሉ ከዓመት በፊት ያሉትን ደግመውታል።

ኮሚሽኑ ባለፉት ዓመታት የገጠሙትን ከፍተኛ ችግሮች እና አሁንም እየፈተኑኝ ነው ያላቸውን አራት ጉዳዮችን ለይቶ ለምክር ቤቱ አቅርቧል። ኮሚሽኑ ገጠሙኝ ያላቸውን ፈተናዎች በዋናነት ከሠላምና ጸጥታ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ለምክር ቤቱ የተበተነው ሪፖርት ያመላክታል። የምክክር ኮሚሽኑ አጀንዳ በማሰባሰብ ሂደት ተለዋዋጭ እና ፈታኝ ተግዳሮቶች እንደገጠሙት በሪፖርቱ ገልጧል። ሥራው በበርካታ ፈታኝ ሁኔታዎች የተሞላ መሆኑን የገለጠው ኮሚሽኑ፣ በተለይም የግጭት ተጽእኖ ቀዳሚው ነው ብሏል። ኹለተኛው ኮሚሽኑ ገጥሞኛል ያለው ፈተና ከነጻነትና ገለልተኝነት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው ብሏል። ከኮሚሽኑ ነጻነትና ገለልተኝነት ጋር በተያያዘ የተዛቡ መረጃዎች ስርጭት ከፍተኛ ፈተና መሆኑንም በሪፖርቱ ተገልጧል። አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች በራሳቸው ሲል ኮሚሽኑ በጠራቸው ምክንያቶች በምክክር ሂደቱ አለመሳተፋቸው ተግዳሮት እንደሆነበትም ጠቁሟል። በአራተኛነት የተቀመጠው የኮሚሽኑ ፈተና የታጠቁ ቡድኖች ተሳትፎ አለመኖር ነው። በትጥቅ ትግል ውስጥ ያሉ ወገኖችን ለማሳተፍ ምቹ ሁኔታ አለመኖሩ፣ ከፍተኛ ተግዳሮት እንደሆነበት ኮሚሽኑ ለምክር ቤቱ ባቀረበው ሪፖርት አስታውቋል። ኮሚሽኑ የታጠቁ ቡድኖች በምክክር ሂደቱ እንዲሳተፉ ለማስቻል ዝግጁነት እንዳለው የገለጠ ቢሆንም፣ ተጨባጭ ውጤት ለማምጣት ግን ከመንግሥት እና ከታጣቂ ቡድኖች ተጨማሪ ጥረቶች ያስፈልጋሉ ብሏል።

## ትችቶቹ ምንድር ናቸው?

በዚኽ ንዑስ ርዕስ ስር ጠቅለል አድርገን ልንጠቅሳቸው የምንሻቸው ትችታዊ ነጥቦች፣ በቀጣይ ኮሚሽኑን ለሚቆጣጠረው የኢንደራሴዎቹ ምክር ቤትም ሆነ ለኮሚሽኑ ፋይዳ ይኖራቸዋል ብለን እናምናለን፣ አጠር አድርገን እናነሳቸው።

- ተዓማኒነትና ገለልተኝነት፦ አንዳንድ የኮሚሽኑ አባላት ከገዥው ብልጽግና ፓርቲ ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል በተለያዩ የተፎካካሪ ፓርቲዎች እና አንዳንድ ተንታኞች ዘንድ በጥርጣሬ ሲነሳ ይስተዋላል። ኮሚሽነሮቹ የተመረጡበት ሂደትም ግልጽነት የጎደለው እና ተቃዋሚዎችን ያላሳተፈ ነው በሚልም ጥያቄ ይነሳበታል።

- የፖለቲካ መጠቀሚያ የመሆን ስጋት፦ የብልጽግና መንግሥት ኮሚሽኑን ሥልጣኑን ለማቆያ፣ የዓለም ዓቀፉን ማኅበረሰብ ድጋፍ እና ብድር ለማግኛ እንደ መሣሪያ እየተጠቀመበት ነው የሚል ክስም ይሰማል።
- ወንጀሎችን የመሸፋፈን ሙከራ፦ መንግሥት በአማራ፣ በትግራይ እና በወለጋ አካባቢዎች ላይ ተፈጽመዋል የሚባሉ የጦር ወንጀሎችን እና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በምክክሩ ሰበብ ለመሸፈን እየሞከረ ነው የሚል ጠንካራ ትችትም ይነሳል።
- የአካታችነት ጉድለት፦ ትርጉም ላለው የሰላም ሂደት ወሳኝ የሆኑ ዋና ዋና የፖለቲካ ኃይሎችን እና የታጠቁ ቡድኖችን ወደ ምክክሩ ለማምጣት መንግሥትም ሆነ ኮሚሽኑ በቂ ጥረት አላደረገም የሚል ቅሬታ አለ።
- በቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮር፦ ኮሚሽኑ ለግጭቶች መንስኤ የሆኑትን መሠረታዊ የፖለቲካ ችግሮች ከመፍታት ይልቅ፣ በቴክኒካዊ እና በሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች ላይ መጠመዱ ችግሩን ለመፍታት ያለውን ቅንነት ጥያቄ ውስጥ ከቶብናል የሚሉ ድምጾችም ይደመጣሉ።

## የብሪጅ ምክረ-ሐሳቦች

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ፊት የተጋረጡት ችግሮች ለኢትዮጵያ ብቻ ለየት ብለው የተከሰቱ አይደሉም። ታሪክ እንደሚያሳየው መዋቅራዊ ድክመቶች፣ አለመተማመን እና በልሂቃን መጠለፍ የተነሳ በሌሎች አገራትም ብሔራዊ ምክክሮች በተደጋጋሚ ለውድቀት ተዳርገዋል። በደቡብ ሱዳን የሰላም ግንባታ ሂደት ልሂቃንን በማግለል፣ በታሪካዊ ቅሬታዎች እና በብሔር ክፍፍል ምክንያት ተስፋ የተደረገበት አገራዊ ምክክር ተሰናክሏል። በሌላ በኩል በላይቤሪያ ከጦርነት በኋላ የመጣው ዕርቅ አሉታዊ ሰላም ብቻ ሆኖ ቀርቷል፤ ይህም በመንግሥት እና በተቃዋሚዎች ለፖለቲካ ትርፍ ሲባል ለትጥቅ መፍታት መዘግየት እና ላለመተማመን ምክንያት ሆኗል። የመን፣ ቻድ እና ስሪላንካም ተመሳሳይ የክሽፈት ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ሁኔታዎች የሚያረጋግጡት አንድ መራራ እውነት አለ፤ ያለ አካታች ተወካዮች፣ ያለ ተቋማዊ ነፃነት እና ያለ ገለልተኛ የአፈጻጸም ሥርዓት እጅግ ተስፋ ሰጪ የሚባሉ ምክክሮች እንኳን መክሸፋቸው። ከዚኽ አንጻርም፣ ብሪጅ ተከታዮቹን ነጥቦች በምክረ-ሐሳብ ደረጃ ለማቅረብ ትሻለች። ወደ ጥቅል ምክረ-ሐሳቦች ለመሄዳችን በፊት ግን፣ የአንደራሴዎቹ ምክር ቤት በዚኽ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ይኖርበታል ብለን የምናምናቸውን ሐሳቦች አጠር አድርገን እንጥቀስ፡

እንደ ብሪጅ መረዳት፣ የአንደራሴዎቹ ምክር ቤት ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽንን በዐዋጅ ያቋቋመ የበላይ አካል እንደመሆኑ መጠን፣ ሂደቱ ስኬታማ እንዲሆንና አመኔታ እንዲያገኝ የሚከተሉት ወሳኝ ሚናዎች ሊኖሩት ይገባል፦

- የክትትል እና የቁጥጥር ሚና፦ ምክር ቤቱ ኮሚሽኑ ሥራውን በገለልተኝነት እና በአካታችነት እያከናወነ መሆኑን እስከ አኹን ካደረገው በላይ በቅርበት መከታተል ይኖርበታል፤ ስለምን ቢሉ፣ ከዚኽ በኋላ ያሉት የኮሚሽኑ ጊዜያት እጅጉን ወሳኝ ናቸውና።
- የኮሚሽኑን አፈጻጸም ሪፖርት መገምገም፦ ምክር ቤቱም ሆነ የሚመለከተው የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ኮሚሽኑ በየጊዜው የሚያቀርባቸውን ሪፖርቶች ሲገመግም፣ በዝግጅት እና በሂደት ምዕራፎች የታዩ የአካታችነት ጉድለቶች እንዲታረሙ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል እንላለን።
- የኢፌድሪ የአንደራሴዎች ምክር ቤት፣ ቀዳሚ ህልውናውን የሕዝብ ውክልና ነውና፣ ኮሚሽኑ ከአድሎአዊነት ነፃ መሆኑን እና ለሕዝብ ግልጽ መሆኑን ሳያሳልስ ለማረጋገጥ ከዚኽ ይበልጥ መጣር ይኖርበታል እናላለን።
- ኮሚሽኑ በተደጋጋሚ ካነሳቸው ተግዳሮቶቹ ዋነኛው፣ ታጣቂ ኃይሎችን ለማሳተፍ መቸገሩ መሆኑ ይታወቃል፤ ከዚኽ አንጻርም፣ ምክር ቤቱ ለታጣቂዎቹ የሕግ ከለላ የሚሰጥበትን መላ ቢያበጅ፣ የታጠቁት ቡድኖች ያለ ስጋት በምክክሩ እንዲሳተፉ የሚያስችላቸው ይመስለናልና፣ ቢታሰብበት ስንል የዜግነት ኃላፊነታችንን ተንተርሰን ጥሪ ማድረግ እንፈልጋለን።

ሌላይኛው የምክረ-ሐሳባችን ማጠንጠኛ ራሱ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ሲሆን፣ ጥቂት ሐሳቦችን ማዋጣት ደግሞ ተቋማዊ ኀላፊነታችን ነውና፣ የሚከተሉትን ነጥቦች ኮሚሽኑ ቢመለከታቸው ቀሪ ሥራዎቹን ያቀልለታል ብለን እናምናለን።

- እስከ ዛሬ ድረስ ኮሚሽኑ የተከተለው የተሳታፊዎች የመረጣ ስልት፣ ከታች ወደ ላይ የሚሄድ አካሄድን መሆኑ ይታወቃል። ይኽ የአመራረጥ ስልትም፣ የየአካባቢዎችን እውነተኛ የግጭት መንስኤዎች እና ተዋናዮችን ችላ ይላል የሚሉ ስጋቶችን ተቋማችን ታዝባለች። ተሳታፊዎችን ወረዳ ጀምሮ መምረጥ በቡድኖች መካከል ያለውን አግድምዮሽ ግጭቶች እና ቁርሾዎች ይሸፍናል የሚል ተያያዥ ስጋትም አለ። ይኽ አካሄድም ዋና ዋና የግጭት ተዋናዮች ሳይካተቱ እንዲቀሩ ያደርጋልና፣ ባሉት ስምንት ወራት ይኽን ተቋማዊ አካሄድ ኮሚሽኑ በቻለው ልክ ለማስተካከል ቢጥር ፋይዳው ብዙ ነው እንላለን።
- ኮሚሽኑ ተሳታፊዎችን በዘጠኝ የኅብረተሰብ ዘርፎች የመደበበት መንገድም እንዲኹ ከትችት አላመለጠም። ስለምን ቢሉ፣ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ቀውስ መሠረት ነው የሚባለውን የብሔር እና የሃይማኖት ማንነትን ግምት ውስጥ አላስገባምና። በተለይም፣ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግር በብሔርተኝነት እና በማንነት ፉክክር ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ፣ ተሳታፊዎቹን በሙያ ወይም በኑሮ ኹኔታ ብቻ ማቧደን ይህንን መሠረታዊ ችግር ችላ ይላል። እናም፣ ኮሚሽኑ ይኽንን ተቋማዊ ዝንፈትም ቢያርመው በጎ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ስትል ብሪጅ ምክረ-ሐሳቧን ማቅረብ ትሻለች።
- የተቋማት ቅሬታም ሲነሳ ይሰተዋላል፤ ለማሳያ ያህልም፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተገልያለሁ በሚል ቅሬታ ማቅረቧ ይታወሳል። ከዚኽ አንጻርም፣ ኮሚሽኑ እንደ ሃይማኖት እና ብሔር ያሉ የማንነት ስብስቦችን እንደ አንድ የጋራ አካል ማሳተፍ አለመቻሉን ያሳያልና፣ ይኽም እርምት የሚደርግበት ኹኔታ ቢፈጠር፣ ኮሚሽኑ ላይ ያለው ሕዝባዊ ተስፋ ወደ መሬት ይወርዳልና ቢታስብበት እንላለን።
- አጀንዳዎችን አለመተው አልያም አለማቅለል፤ ኮሚሽኑ አጀንዳ የማስተካከል ሕጋዊ ሥልጣን ቢኖረውም፣ ከተሳታፊዎች እና ከተለያዩ ወገኖች የሚቀርቡ አጀንዳዎች ተቀባይነት እንዲያገኙ እና ያለ አግባብ እንዳይጣሉ ማረጋገጥ ይኖርበታል፤ ይኽንንም፣ ይፋዊ እና ሕዝባዊ መድረኮችን በመጠቀም ቢከውናቸው የተቋሙን ተዓማኒነት ከፍ ያደርጋልና፣ ቢታሰብበት ስትል ብሪጅ መጥቀስ ትፈልጋለች።

ከላይ በምክረ-ሐሳብ ደረጃ ያነሳሳናቸውን ምክረ-ሐሳባዊ ነጥቦችንም፣ በሚከተለው አጭር ሰንጠረዥ ጠቅለል አድርገን በማቅረብ፣ የወሩን የብሪጅ ዳሰሳ እናገባድ፤

**የምክክሩን ሂደት የሚያሳልጡ ቁልፍ ተግባራት**

| የትኩረት መስክ | መወሰድ ያለበት እርምጃ | የሚጠበቅ ውጤት |
|---|---|---|
| **አካታችነት** | የታጠቁ ቡድኖችን እና ያልተካተቱ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን በምልዓት ማሳተፍ፤ | የጦርነት መቆም እና ሰፊ ፖለቲካዊ ተቀባይነት ማስፈን፤ |
| **ግልጽነት** | የተሳታፊዎችን ዝርዝር፣ የአጀንዳ አሰባሰብ ሂደቱን እና አጀንዳዎቹን በዝርዝር ይፋ ማድረግ፤ | በሕዝብ እና በባለድርሻ አካላት ዘንድ አመኔታ መጨመር፤ |
| **ተጠያቂነት** | አለ ተብሎ በተለያዩ ወገኖች የሚነሳውን የመንግሥትን ተጽዕኖ መቀነስ እና ገለልተኛ አሠራር ለመኖሩ ሕዝባዊ ይኹንታ እንዲገኝ መሥራት፤ | የምክክሩ ውጤት ተዓማኒ እና ተግባራዊ ማድረግ፤ |

## ፍካሬ ዘ እንደራሴ

“እንደራሴ” የሚለው ንባበ-ቃል በኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ የፖለቲካ ተዋስዖ እና የሥነ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ግዝፈት የነሳ ፍካሬያዊ ንባበ-ቃል ነው። የቃሉ ከየት መጥነት እና ፍካሬም፣ በአጠቃሎ መልኩ ይኽን መሰል ፍቺዎች ነበሩት/አሉትም።

ንባበ-ቃሉ የተገኘው “እንደ” እና “ራሴ” ከሚሉ የኹለት ቃላት ጥምረት ነው። “እንደ”፦ መስያ፣ ፈንታን ወይም ምትክን ሲያመለክት፤ “ራሴ”፦ ራስ ጠሪውን ማንነት አልያም ባለቤቱን-ሲፈከርም ባለሥልጣኑን ያነጽራል። በአማሪያዊ ፍቺውም፣ “እንደ እኔ” ወይም “እኔን ሆኖ” ማለት ነው ይኋል። በኢትዮጵያ ሥነ-መንግሥት ታሪክ “እንደራሴ” የሚለው ማዕረግነቱን ሲያጣቅስ፣ በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነበረው፤ ለማሳያ፦

ሀ- የንጉሠ ነገሥቱ ተወካይ (በፈረንጅ አፍ- Regent እንዲሉ)፦ በንጉሣዊው ሥርዓት ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ በአንዳች ምክንያት (ለዐቅመ-መንበር ባለመድረስ፣ በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት) አገረ-መንግሥቱን መምራት ካልቻሉ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶት አገሪቱን የሚያሥተዳድረው ሰው “ቢትወደድ-እንደራሴ” ይባል ነበር።

ለ- የአካባቢ ወይም የክፍለ-ሀገር ገዢነት፦ ንጉሠ ነገሥቱ በየክፍለ ሀገራቱ ‘ራሳቸው ዘወትር መገኘት ስለማይችሉ፣ በ‘ርሳቸው ስም የሚፈርዱ እና የሚያሥተዳድሩ ተወካዮቻቸውን “እንደራሴ” ይኋቸዋል፤ ይኽም የንጉሡ ምሉዕ ተወካይነትን ይሰጣል።

ሐ-የሕዝብ እንደራሴነት፦የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ከመጣ ወዲኽ ግን ቃሉ አዲስ ፍካሬ ያዘ። ሕዝቡ በ‘ራሱ ፈንታ ሆኖ በምክር ቤት እንዲመክርለት እና ውሳኔም እንዲሰጥለት የሚመርጣቸው ሰዎች “የሕዝብ እንደራሴዎች” መባል ጀመሩ። የዚኽ ፍካሬም፣ “ሕዝቡን ሆኖ የሚሠራ”፣ “ምስለ-ሕዝብ” አልያም “የሕዝቡ ተወካይ” የሚል ትርጓሜን አሰጠው።

ዛሬ “ተወካይ” (በምዕራቡ የምክር ቤት ታሪክ ጅማሮ-Representative-እንዲሉ) ከሚለው ቃል ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ ያገለግላል። ሆኖም “እንደራሴ” የሚለው ቃል ከውክልና ባለፈ፣ የወከለውን አካል ሙሉ ክብር እና ማንነታዊ ተዛምዶ ይዞ የሚገኝ ክብደት ያለው ፖለቲካዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ፍካሬ አለው።

## የብሪጅ አፈካከር

ተቋማችን ብሪጅ፣ የአማርኛን ሰዋስው ደንብ ጠብቃ፣ ይኽንን ቃል ከኋለኛው ወደዚኽ ዘመን አናጥቃ በመፈከር ተጠቅማለች። አስቀድመን ሊቃውንቱ ያስቀመጡትን እንጥቀስ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፣ እንደ ራሴ፣ እኔን ሆኖ፣ የእኔን ሥልጣን ይዞ የሚሠራ ብለው ሲፈቱት፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በፈንታ፣ በምትክ የሚቆም ሲሉት፤ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጸው በተራቸው፣ ተለዋጭ፣ ተወካይ፣ ባለሙሉ ሥልጣን የሚል ፍቺ ይሰጡታል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልም ቢሆኑ፣ አንድ ሰው በራሱ ስም ሳይሆን በሌላው ስም ተገኝቶ የሕግ ተግባራትን ሲያከናውን እንደራሴ መባሉን ያነሳሉ። እነዚኽ ዋቢዎች እንደሚያሳዩት፣ ቃሉ በመጀመሪያ ለነገሥታት ተወካዮች ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ ኋላ ለሕዝብ ተወካዮች እንዲሠራበት የተደረገው የሕዝቡን ልዕልና ለመግለጽ ውለዋል፤ አለፍ ሲልም፣ ተወካዩ ሕዝቡን ሆኖ ይገኛል፤ እንደ ሕዝቡ ሆኖ ይጠራል የሚለውን ፍካሬ ይሰጣሉ።

በዚኽ አግባብ፣ “እንደራሴ” ስንል፦ አንድም ራስ የሚለውን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ከቆመበት ‘የራስን ዕድል በራስ የመወሰን’ ሕገ-መንግሥታዊ ነባር መርህ ጋር አናጽረን ፈክረነዋል። ይኽ ማለት፣ በዚኽ መርህ ውስጥ ያለው ‘ራስ’፣ የሚለው ትርጉም የሚጠቅልላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በ“እንደራሴ” ውስጥ ያለውን ‘ራሴ’ን ለመፍታት ፍካሬያዊ ትርጓሜን ተጠቅመናል። ከዚያ ባለፈም፣ በቀደመው ዘመን መራጩ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነው ሁሉ፣ በዚኽኛው የእኛው ዘመን ሕዝብ ነውና፣ “እንደራሴ” ስንል፦ እንደ መረጠው ሕዝብ፣ ብሔረሰብ አልያም ብሔር የሆነ በሚል ፍቺ መጠቀማችንን ልብ ይኋል። በዘመናዊው የምርጫ ሥርዓት ስናነጽረውም፣ መራጩ ግለሰብ እንደራሴውን ‘ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በመንበሬ’ ሲል፣ በነገረ-ሕይወቱ ይወስንለት ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ መርጦ ይልከዋል። የመረጠውም እንደራሱ ካልሆነለት፣ ምስለ እኔነቱን ሊነጥቀው መቻሉን ያስረግጣል።

የ“እንደራሴ” ንባበ-ቃል፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ሲቋቋም፣ የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ በዘመኑ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው አማርኛ ብቻ ቢሆንም ቅሉ፣ ንባበ-ቃሉ ግን በሌሎቹ የአገራችን የብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎች ውስጥም መገኘቱን ልብ ይኋል፤ ለማሳያ፦ በሲዳማ- amaalete mina፣ በአፋን ኦሮሞ-Bakka bu’aa፣ በትግሪኛ- ከማይ፣ በወላይተኛ Kal Ati-ya/Taga ton መባሉን ያስታውሷል።

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

**አንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።**


BRIDGE Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 99 808 5013

info@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, O ce No. 5, Addis Ababa.